# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 202 መጋቢት 22 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ

# ኢትዮጵያ ወደተሟላ ሰላም

## የምታደርገውን ጉዞ እየደገፈ ነው


ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ
አምባሳደር መለስ አለም

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብና ድርጅቶች ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ ሰላም የምታደርገውን ጉዞ በቁርጠኝነት እየደገፉ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። ኢትዮጵያ ዓባይ ግድብን የጀመረችው ለሙከራ ሳይሆን አጠናቆ ለመልማት መሆኑንም አስምሮበታል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም ትናንት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ሚዲያዎች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ ሳምንቱ የሰላምና ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን በማስተሳሰር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ ተሠርቶበታል ብለዋል።

ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብና ድርጅቶች የኢትዮጵያ የሰላም ጉዞ ተስፋ ሰጪ ነው የሚል ዕምነት እንዳላቸው ገልጸውም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰላም ሂደት ይበልጥ ለማገዝና ለመደገፍ ፍላጎት አላቸው ብለዋል።

ከሰላም አንጻር ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ ሰላም የምታደርገውን ጉዞ በቁርጠኝነት

ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል





ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ
ዶክተር ነገሪ ሌንጮ

# በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል

- ቋሚ ኮሚቴው

# በ8 ወራት ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

- ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ለዜጎች የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ። በስምንት ወራት ለ2 ሚሊዮን 84ሺህ 702 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ።

በሥራ ዕድል ፈጠራ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# በበጋ የምርት ዘመን

## ከ40 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይሰበሰባል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የበጋ የምርት ዘመን ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ ምርት የተሸፈነ በመሆኑ ከ40 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት እንደሚገኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ባለፈው ማክሰኞ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንዳብራሩት፤ ባለፈው

በበጋ የምርት ዘመን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በ10 ዓመታት ሁሉንም ዜጋ የዘመናዊ ኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው

- 98 ሚሊዮን ዜጎች ለምግብ ማብሰያነት አካባቢን የሚበክሉ ግብዓቶችን ይጠቀማሉ



**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአገር አቀፍ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም እስከ 10 ዓመት ድረስ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የዘመናዊ ኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት

በ10 ዓመታት ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል









አቶ ሰለሞን ክቤ




# ትምህርት ቤቱ በዘመናዊ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ሽልማት አገኘ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የደጅ አዝማች ወንድይራድ አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ባከናወነው ሥራ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ ሽልማት አገኘ። ትምህርት ቤቱ በከተማ ግብርና ተሸላሚ እንደሆነም አስታውቋል።

የደጅ አዝማች ወንድይራድ አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ሰለሞን ክቤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ትምህርት ቤቱ የዘመናዊ ደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት ባከናወነው ተግባር ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዓለም አቀፍ ሽልማት ማግኘት ችሏል።

ትምህርት ቤቱ የአየር ንብረት ለውጥን የሚከላከል ተስማሚ እና መልሶ የመጠቀም አሠራርን የያዘ የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት ለአረንጓዴና ጤናማ የከተማ ግንባታ ሂደት እና ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት በመቀየር ለገቢ ማስገኛ ሥራ በማዋሉ በመልካም ተሞክሮ ተሸላሚ መሆን ችሏል ነው ያሉት።

ትምህርት ቤቱ በቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት የብዙዎችን ሕይወት ሊታደግ የሚችል እና በከተማ እየተከናወነ ላለው የጓሮ አትክልት ልማት ሥራ ማዳበርያ ማቅረብ ያስቻለ የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋቱ ለእውቅና እንዳበቃው ርዕሰ መምህሩ ጠቅሰዋል።

እንደ ርዕሰ መምህሩ ገለፃ፤ በትምህርት ቤቶች በጠባብ ቦታ ላይ እየተተገበረ ያለው የከተማ ግብርና በአንድ በኩል ምርቱ ለተማሪዎች ምገባ እንዲውል የታለመ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቆሻሻን ተማሪዎች ወደ ኮምፖስት መቀየር የሚያስችል ዕውቀት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው። ይህ ሂደት ተፈጥሮን የሚያከም ቆሻሻን ወደ ሀብትነት የቀየረ በመሆኑ ትምህርት ቤቱ ሽልማት ማግኘት ችሏል።

በከተማ ግብርና፣ አረንጓዴ ልማት፣ የተቀናጀ ፅዳትና ውበት እና የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ትምህርት ቤቱ ሽልማት ያገኘባቸው ዘርፎች ናቸው ያሉት መምህር ሰለሞን፤ የደጅ አዝማች ወንድይራድ ትምህርት ቤት የአምስት ዓመት የከተማ ግብርና ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ነው ብለዋል።

በግብርና ፍኖተ ካርታው የመጀመሪያው ዓመት የጓሮ አትክልት፤ በሚቀጥለው ዓመት ዶሮ፣ በሌሎቹ ዓመታት ደግሞ የዓሣ፣ ንብ ማነብና የእንስሳት ርባታ የያዘ ነው ያሉት ርዕሰ መምህሩ፤ አሁን ላይ ትምህርት ቤቱ የግብርና ውጤቶችን ከራሱ አልፎ ለአካባቢው ማህበረሰብ እያቀረበ ይገኛል። በዚህም በወር በአማካኝ ከ18 ሺህ ብር በላይ ገቢ እየተገኘ ነው ብለዋል።

ፕሮጀክቱን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከኦስትሪያ ቪየና ከተማ ጋር በመተባበር የሚያንቀሳቅሰው ነው። በዚህም የደጅ አዝማች ወንድይራድ አፀደ ሕፃናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሳየው ንቁና ጠቃሚ ተሳትፎ የተበረከተ እንደሆነ በሽልማት ሰርተፍኬቱ ተገልጿል።

# የዓባይ ግድብ የተጋረጡብንን ፈተናዎች መወጣት እንደምንችል ማሳያ ነው ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ም/ፕሬዚዳንት ገለጹ

## - የግድቡ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት 12ኛ ዓመት በኦሮሚያ ክልል ተከብሯል

**ገመቹ ከድር**



አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ የተጋረጡብንን ፈተናዎች በሕዝባችን ድጋፍ መወጣት እንደምንችል ትልቅ ማሳያ ነው ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት አወሉ አብዲ ገለጹ። የዓባይ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠበት 12ኛ ዓመት በኦሮሚያ ክልል ደረጃ በአርሲ ዞን በፎቶ አውደ ርዕይና በፓናል ውይይት ተከብሯል።

የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አወሉ አብዲ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ለማብቃት ሕዝቡና የለውጡ አመራር የማይተካ ሚና መጫወቱን ገልጸዋል።

በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት ዘርፈ ብዙ ፈተናዎችን በመቋቋም የግድቡ ግንባታ ለአፍታም ሳይቋረጥ በተጠናከረ መልኩ ማስቀጠል መቻሉን ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ክልል ሕዝብ የዓባይ ወንዝ ለዘመናት ሳይለማ የባዕድ አገር ሲሳይ ሆኖ መቆየቱ ባሳደረበት ቁጭት የግድቡ ግንባታ ከዳር እንዲደርስ ርብርብ እያደረገ ነው ብለዋል።

የክልሉ ሕዝብ ከመንግሥት ጋር በመሆን ለግድቡ ተሳትፎ ከ4ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል ያሉት አቶ አወሉ፤ ፕሮጀክቶችን መሠረት ድንጋይ ለማስቀመጥ ሳይሆን በማጠናቀቅ ለሕዝብ አገልግሎት ለማዋል እንሠራለን ብለዋል።

ሕዝቡ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ ዘንድሮም በተፋሰስ ልማትና በቦንድ ግዢ እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠሉንም አመልክተዋል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ዶክተር አረጋዊ በርሔ በበኩላቸው ሕዝቡ በግድቡ ላይ በውጭ ሚዲያዎች የሚደረገውን ዘመቻና በአገር ውስጥ የነበሩ ችግሮች ሳይበግሩት ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸዋል።

«ኢትዮጵያ አስቸጋሪ ፈተናዎች ውስጥ በነበረችበት ወቅት የኦሮሚያ ክልል ያደረገው ድጋፍ ዳግም ኢትዮጵያዊ ጀግንነቱን ያረጋገጠ ነው» ብለዋል።

አሁንም ቀሪ የግንባታ ሂደት እስኪጠናቀቅ ሕዝቡ የጀመረውን ሁሉን አቀፍ ርብርብ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

የኦሮሚያ ክልል የዓባይ ግድብ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ቆንጂት በቀለ የክልሉ ሕዝብ በ12 ዓመታት ውስጥ ከ4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር በላይ በቦንድ ግዥና በስጦታ ድጋፍ ማድረጉን ገልጸዋል።

12ኛ ዓመቱን በማስመልከት የተዘጋጀው የቦንድ ሽያጭ በክልሉ እየተከናወነ እንደሚገኝና እስከ አሁን ከ42 ሚሊዮን ብር በላይ ለግድቡ ግንባታ በቦንድ ግዥና በስጦታ ገቢ መሰብሰቡን ገልጸዋል። ግድቡ በደለል እንዳይሞላ ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሰዎች በአረንጓዴ አሻራ ልማት መሳተፋቸውንም ገልጸዋል።

በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ 12ኛ ዓመት በዓል ላይ ባለሀብቶችን ጨምሮ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳታፊ ሆነዋል።




ፎቶ፡ አዮብ ተፈራ

# ባለሥልጣኑ የደንብ ማስከበር ችግሮችን ለመከላከል ርምጃ እየወሰደ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ የሚስተዋሉ የደንብ ማስከበር ችግሮችን ለመከላከል የተጠናከረ ርምጃ እየወሰደ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ገለጸ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ከሰላምና ፀጥታ አመራሮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁም ተፈራ፤ ከመሬት ወረራ፣ ከሕገወጥ ንግድና ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የደንብ ማስከበር ችግሮች መከሰታቸውንና የማስተካከያ ርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል።

በበጀት አመቱ ስድስት ወራት ውስጥ ሕገወጥ ድርጊቶች ፈጸመው የተገኙ አካላት ላይ በተወሰደ እርምጃ 11 ሚሊዮን 704 ሺህ ብር በቅጣት እንዲሁም ከጨረታ ገቢ አራት ሚሊዮን 262 ሺህ 41 ብር ተገኝቷል። በአጠቃላይ የተገኘው ገቢም 15 ሚሊዮን 269 ሺህ 447 ብር ሆኗል ብለዋል።

በተጨማሪም ከ 1 ነጥብ 1 ሚሊዮን በላይ ኅብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የደንብ መተላለፍን ችግር ለመከላከል የሚረዳ የግንዛቤ ማስጨበጫና ውይይት መድረክ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

የባለስልጣኑ የደንብ መተላለፍ ግንዛቤ ማስጨበጫ ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰርካለም ፋንታሁን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ ግማሽ አመት በአጠቃላይ 127 ሺህ 218 ደንብ መተላለፎች ላይ ርምጃ ለመውሰድ ታቅዶ 263 ሺህ 907 ሕገወጥ ሥራዎች ላይ ሕጋዊ ርምጃ ተወስዷል።

35 ሺህ 154 ሕገወጥ የጎዳና ንግድ፣ 5 ሺህ 654 የሕገወጥ የመሬት ወረራ፣ 3 ሺህ 635 የሕገወጥ ግንባታ፣ 677 ሕገወጥ የመሬት ማስፋፋት፣ 587 ሕገወጥ የእንስሳት እርድ፣ 1 ሺህ 727 ሕገወጥ አዋኪ ድርጊቶች፣ 5 ሺህ 35 ሕገወጥ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ 6 ሺህ 553 ሕገወጥ የመንገድ አጠቃቀም እና 204 ሺህ 898 ሕገወጥ ማስታወቂያዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ተወስዷል ብለዋል።

በቀጣይም በከተማው የተጀመረውን የደንብ ማስከበር ሥራ ከፀጥታና ፍትህ ተቋማት እንዲሁም 13 የሚሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራበት መሆኑን ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰላም፣ የፍትህ እና መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ እንደገለጹት፤ በከተማው የሚስተዋለው የሕግ ጥሰት ትውልድን እንዲሁም አገርን ወደኋላ የሚጎትት ነው።

በዋነኝነት የአዋኪ ድርጊቶች መበራከት፣ ሐገወጥ የመንገድ ንግድ መበራከትና የመሬት ወረራ ለከተማ አስተዳደሩ ትልቅ እንቅፋት ነው ያሉት አቶ ሙሉነህ፤ የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ከአጋር ተቋማት ጋር እያከናወነ ያለውን ተጨባጭ እንቅስቃሴ አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አሳስበዋል።

# ምክር ቤቱ የዲጂታል መታወቂያ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጸደቀ

## - የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲን በተመለከተ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ለቋሚ ኮሚቴ መርቷል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2ኛ አመት የሥራ ዘመን 12ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ረቂቅ አዋጅን ጨምሮ የተለያዩ አዋጆችን አጸደቀ። ስለራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲና የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና የምርምር ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስርን ለመደንገግ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅና ሌሎች አዋጆችንም መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2ኛ አመት የሥራ ዘመን 12ኛ መደበኛ ስብሰባው የምክር ቤቱን 6ኛ አመት የሥራ ዘመን 1ኛ ልዩ ስብሰባ 11ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤን መርምሮ አጽድቋል።

ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ ዲጂታል መታወቂያ አዋጅን አስመልክቶ የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና የሰው ሀብት ልማት፣ የሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩል የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ አጽድቋል።

የውሳኔ ሃሳቡን ያቀረቡት የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ እፀገነት መንግሥቱ፤ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት ሁሉን አቀፍ፣ ወጥና አስተማማኝ የአገሪቷ ነዋሪዎች የሚመዘገቡበት ሥርዓት በመዘርጋትና የተመዝጋቢዎችን መረጃ በመያዝ የዲጂታል መታወቂያ አጠቃቀም ሥርዓትን ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው የሚያደርግ ነው ብለዋል። ምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳቡን ካዳመጠና ከተወያየ በኋላ ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1284/2015 አድርጎ በአንድ ድምፀ ተአቅቦ በአብላጫ ድምፅ አፅድቋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ መንግሥትና በዓለም አቀፉ የልማት ማሕበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት አዋጅ መርምሮ አጽድቋል። የብድር የስምምነቱን የውሳኔ ሃሳብና ሪፖርቱን ያቀረቡት የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ደሳለኝ ወዳጆ፤ የብድር ስምምነቱ ዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮጀክትን በማስፈፀምና የመሬት ልማት ሥራዎችን ለመሥራት፣ ዘመናዊ የመሬት አያያዝን ለማስፈን ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ባቀረቡት ማብራሪያ ገልጸዋል። ምክር ቤቱም የውሳኔ ሃሳብ ሪፖርቱን ካዳመጠ በኋላ የብድር ስምምነቱን አዋጅ ቁጥር 1285/2015 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል።

ምክር ቤቱ ስለ ራስገዝ ዩኒቨርሲቲዎች የቀረበውን ረቂቅ አዋጅና የከፍተኛ ትምህርት፤ ቴክኒክና ሙያ ስልጠኛ፤ የምርምር ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ ለዝርዝር እይታ ለሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተባባሪነት ደግሞ ለሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

በረቂቅ አዋጁ ዙሪያ ማብራሪያ የሰጡት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ፤ ዩኒቨርሲቲዎቹ ራስገዝ እንዲሆኑ መታሰቡ ለተቋማት ውጤታማነት፣ ተቋማቱ ነፃነት እንዲኖራቸው፣ የራሳቸውን የገቢ ምንጭ እንዲያስፋፉ እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። በተመሳሳይም የከፍተኛ ትምህርት፤ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የሚቀርጿቸው የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች የኢኮኖሚውን ውጤታማነት ለማሳደግ በትስስር እንዲሠሩ ለማስቻል የቀረበ የውሳኔ ሀሳብ ነው ብለዋል።

ምክር ቤቱም በጉዳዩ ዙሪያ በስፋት ከተወያየበት በኋላ ረቂቅ አዋጁ አዋጅ ቁጥር 16/2015 ሆኖ ለሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተባባሪነት ለሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምፅ ተመርቷል።

በተመሳሳይ ምክር ቤቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት መተዳደሪያ ደንብን ለማዘጋጀት የቀረበ ረቂቅን ረቂቅ ደንብ ቁጥር 02/2015 አድርጎ ለዝርዝር ዕይታ ለሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶታል። በተጨማሪም በኢትዮጵያና በሉግዘንበርግ መንግሥት መካከልና በስዊዝ ኮንፌዴሬሽን መካከል ተደራራቢ ግብርን ለማስወገድና የታክስ ማጭበርበርን ለመከላከል የተደረሰውን የሁለትዮሽ ስምምነት አስመልክቶ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሯል። በዚህም አዋጅ ቁጥር 18/2015 እና አዋጅ ቁጥር 19/2015 አድርጎ ለፕላን በጀትና ፋይናንስ በተባባሪነት ለሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ መርቷል።

ከዚህም ባሻገር ምክር ቤቱ ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት ፈጽመዋል በተባሉ አንድ ዳኛ ላይም የስንብት ውሳኔ አሳልፏል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ እፀገነት መንግሥቱ፤ ከባድ የሥነምግባር ጥሰት የፈጸሙ አቶ ፋንታሁን ደለለው የዳኞች የሥነምግባር ዲስፕሊን ክስ ሥነሥርዓት ደንብ ቁጥር 3/2014 አንቀጽ 6(14) በመተላለፍ ከአመልካች ጋር ከፍርድ ቤት ውጪ ሁለት ጊዜ ተገናኝተዋል።

አንቀጽ 7(2) ላይ የተቀመጠው የሀቀኝነት ተጻራሪ ግዴታ በመተላለፍ ከአመልካች 100 ሺሕ (አንድ መቶ ሺሕ ብር) መደለያ መቀበላቸው በማስረጃ መረጋገጡን ለምክር ቤቱ አቀርበዋል። ዳኛው ጥፋተኛ መሆናቸውን ቋሚ ኮሚቴው መመርመሩን አብራርተው የውሳኔ ሂደቱ የዳኛውን የመደመጥ መብት ያከበረና ማስረጃን መሠረት ያደረገ ነው። ስለሆነም ምክር ቤቱ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሪፖርት ካዳመጠ በኋላ የአቶ ፋንታሁን ደለለው ሽፈራውን የሥራ ስንብት የውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 13/2015 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል።

# የሙከራ ትግበራው ምርታማነት እንዲጨምር ማስቻሉ ተገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የተሻሻሉ የማሽላ ዝርያዎችን በመጠቀም ለሦስት ዓመታት የተከናወነው የሙከራ ትግበራ አርሶ አደሩ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሳደግ፣ ምርታማነትንም በመጨመር ከፍጆታ አልፎ ለገበያ እንዲያቀርብ ማስቻሉን የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የሰብል ምርምር ዳይሬክተሩ ዶክተር ታዬ ታደሰ ባለፉት አራት ክረምቶች ከፍተኛ የማሽላ አብቃይ በሆኑት አማራ፣ ኦሮሚያ እና ትግራይ ክልሎች ላይ የተደረገው የሙከራ ትግበራ አርሶ አደሩ ግንዛቤ መጨበጡን አመልክተዋል።

መርሃ ግብሩ ፈጥነው የሚደርሱ፣ ድርቅን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን ጥቅም ላይ በማዋል አርሶ አደሩን ተጠቃሚ አድርጓል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የውሃ አጠቃቀም እና የማሽላ የስር ዕድገት ባህሪን ለማወቅ አስችሏል፤ ሂደቱን በመገምገም ለማስፋት ይሠራል ሲሉም አመልክተዋል።

መርሃ ግብሩ በተከናወነባቸው ሦስቱ ክልሎች ከዘጠኝ ሺህ በላይ ለሚደርሱ አርሶ አደሮች ቴክኖሎጂዎቹን ለማስተዋወቅ፣ ሁለት ሺ ኩንታል ዘር ብዜትን በማሰራጨት መሠራቱን አመልክተዋል።

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ረጅም ጊዜ የሚቆዩና አርሶ አደሩ ይጠቀምባቸው የነበሩ የማሽላ ዝርያዎች ከምርት እየወጡ እንደሚገኙና የአየር ንብረት ለውጥ ትልቅ ፈተና ሆኖ መቀጠሉንም ተናግረዋል። የወቅቱን የዝናብ እና አፈር ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ የቴክኖሎጂ አማራጮች እንደሚያስፈልጉም ጠቁመዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በሙከራ ትግበራው የማሽላ ምርት ከመሰብሰብ፣ ከመውቃት እና ከማቆየት ጋር በተያያዘ የነበረውን ከፍተኛ ችግር ለመቀነስ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ውጤት ታይቷል። ፈጥነው የሚደርሱና ድርቅን መቋቋም የሚችሉ የማሽላ ዝርያዎች ውጤታማነታቸው ታይቷል።



ዶክተር ታዬ ታደሰ



አርሶ አደር አበበ ቢሰጥ

በግብይት ሰንሰለቱ ውስጥ የሚመለከታቸውን አካላት ተደራሽ በማድረግ፤ ለዘር አቅርቦትና ለአመጋገብ የተሻለ የማሽላ ዝርያ ጥቅም ላይ መዋሉንም ዶክተር ታዬ አመልክተዋል።

የማሽላ ምርት በነቀዝ ሳይበላ፣ በፈንገስ ሳይጠቃ መቆየት እንዲችል ከአምስት ሺ 500 በላይ የምርት ማስቀመጫ ጆንያ በማሰራጨት ለማስተዋወቅ መቻሉንም ጠቁመው፤ በአርሶ አደሩ ዘንድ ፍላጎት መኖሩንና ገበያ እንዲያገኝ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

አንድን ሄክታር ማሳ ለመውቃት አንድ አርሶ አደር ሙሉ ቀን ያስፈልገዋል። ነገር ግን በምርምር በቀን እስከ አራት ሄክታር መውቃት የሚችል አዲስ የተመረተ ማሽን በመኖሩ በተለያዩ አማራጭ መንገዶች ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ ለማድረግ ይሠራል ብለዋል።

በምርምር ከሦስት እስከ አራት ወራት የሚደርሱ ዝርያዎች ቢኖሩም ዝርያዎች ወደ አርሶ አደሩ አልደረሱም። ከ70 በመቶ በላይ አምራች አርሶ አደሮች ለፍጆታቸው እንጂ ለገበያ ስለማያመርቱ በምርት ሂደት ውስጥ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተት አለ። የኮቪድ ወረርሽኝና ጦርነት ለትግበራው ፈተና እንደነበሩም አመልክተዋል።

በሙከራ መርሃ ግብሩ ከተሳተፉት መካከል ከአማራ ክልል ራያ ቆቦ ወረዳ የተወከሉት አርሶ አደር አበበ ቢሰጥ በምርምሩ ከመታገዛቸው በፊት አናሳ ምርት ያገኙ እንደነበር አስታውሰዋል።

‹‹በምርምሩ በመታገዝ ባለፉት ሦስት ዓመታት በሄክታር 60 ኩንታል በማምረት ብዙ ምርት አግኝተናል፤ የማዳበሪያ፣ የዘር ድጋፍ፣ ምርቱ በነቀዝ እንዳይበላ የምርት ማስቀመጫ ጆንያ እናገኛለን። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቃሚ ሆነናል›› ሲሉም ገልጸዋል።

205 አርሶ አደሮች በጋራ በኩታ ገጠም 66 ሄክታር የተሻሻለ የማሽላ ዝርያ ማምረታቸውን በመጥቀስም የመውቂያ ማሽኖችና የማዳበሪያ እጥረት ላይ ድጋፍ እንዲደርግላቸው እንደሚፈልጉም ጠቁመዋል።



# የሽግግር ፍትህ ለዘላቂ ሰላምና ደህንነት ትልቅ ርምጃ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የሽግግር ፍትህ ለዘላቂ ሰላምና ደህንነት ትልቅ ርምጃ በመሆኑ ተነሳሽነቱን እንደ ትልቅ ርምጃ እንደሚያይ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት አስታወቀ። ለሽግግር ፍትህ መሳካት የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ላይ መሥራት እንደሚገባም ተመላክቷል።

በኢትዮጵያ ተግባራዊ በሚደረገው የሽግግር ፍትህ የተቀናጀ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ምክር ቤት የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ ግብር ትናንት ተከናውኗል።

በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ፕሮግራም ዴቨሎፕመንት ዳይሬክተር ሃና ወልደ ገብርኤል በወቅቱ ባደረጉት ንግግር፤ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ በፍትህ ሚኒስቴር አማካኝነት ተዘጋጅቶ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት መጀመሩን በማስታወስ፤ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ተነሳሽነቱን እንደ ትልቅ ርምጃ የሚያይ መሆኑን ገልጸዋል።

ዳይሬክተሯ እንዳሉት፤ ከእርስ በእርስ ጦርነትና ግጭት ወደ ሠላም የመጡና ዴሞክራሲን የገነቡ አገራት የከፋ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ላይ እልባት ለመስጠትና መዋቅራዊ በደሎችን ለማስቀረት የሽግግር ፍትህ ሂደትን ይተገብራሉ።

የሽግግር ፍትህ በተለያዩ ወቅቶች ለተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ፍትህ የሚገኝበት፣ ዜጎች ሁለንተናዊ መልስ የሚያገኙበትና የተፈጸሙ ጉዳዮች እውነት የሚወጣበት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቁርሾዎች የሚታከሙበት እንዲሁም ለመብት ጥሰቶች መነሻ የሆኑ የሚለዩበትና ማህበራዊ ሁኔታዎች የሚሻሻሉበትን ዕድል የሚፈጥር እንደሆነ ጠቅሰዋል። ይህም ለዘላቂ ሠላምና ደኅንነት ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

እሳቤው ፍትህን ለማስገኘት እንዲሁም ሠላምና ዴሞክራሲን ለማስፈንና የእርቅ ዕድሎችን ለማግኘት መልካም አጋጣሚ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የሽግግር ፍትህ ሂደትን ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን በመጠቆም፤ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሠላም ስምምነት የአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፖሊሲን መሠረት ባደረገ መልኩ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ሁሉን አቀፍ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፣ እውነትን የሚያወጣ፣ ተጎጂዎችን የሚክስና እርቅን የሚያሳልጥ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት እንዲዘጋጅ እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ጨምሮ ሌሎች የባለ ድርሻ አካላት ድጋፍ በመስጠት እንዲሳተፉ ጠይቀዋል።

የሽግግር ፍትህ ዓላማ ይሳካ ዘንድም የብዙ ባለ ድርሻ አካላት መነሳሳትና እገዛ ይፈልጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ጉዳዩ በመንግሥት ብቻ ተጀምሮ የሚጠናቀቅ እንዳልሆነና ሂደቱ በርካታ አካላትን የሚመለከት በመሆኑ በርካታ ተዋናንያን ይኖሩታል ሲሉ ገልጸዋል። በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት፣ የሚዲያ ተቋማት ለሽግግር ፍትህ መሳካት የጎላ ሚና እንዳላቸው በመናገር፤ ምክር ቤቱ የተነሳሽነቱን ርምጃ እንደሚደግፈው አስታውቀዋል።

ሽግግር ፍትህ እውን የሚሆነው በሂደቱ ተዋንያን የሆኑ አካላት የሽግግር ፍትህ ጽንሰ ሀሳብን፣ የሌሎች አገራት ተሞክሮዎችን፣ እንዲሁም አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመረዳት ግንዛቤ በተሞላበት መልኩ መረዳት ሲችሉ እንደሆነ አመላክተዋል።

የሽግግር ፍትህ የጥናት ቡድን አባል የሆኑት ዶክተር ማርሸት ታደሰ በመድረኩ ባቀረቡት ጽሑፍ፤ እሳቤው እኤአ በ1980ዎቹ እንደተጀመረ ገልጸው፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በአፍሪካ ህብረት ቅቡልነትን ያገኘ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የሽግግር ፍትህ፤ ተጠያቂነት፣ እውነትን መለየት፣ ተቋማዊ ለውጥ ማምጣት፣ እርቅና ችግሮች እንዳይደገሙ የሚያስችሉ ዓላባዊያን ላይ የተመሠረተ መሆኑን በማንሳት፤ ያለፈውን መጠነ ሰፊ ውስብስብ ጉዳዮችን ለማረም፣ ሁለንተናዊ ፍትህ ለመስጠትና ወደ እርቅ ለመሄድ አስቻይ እንደሆነም ገልጸዋል። ይህም በመርህ ደረጃ ሁሉን አካታች የሆነ ተሳትፎ እንደሚሻ ተናግረዋል።

ዜና

# የሕወሓት ሲቪልና ወታደራዊ አመራሮች ክስ ተቋረጠ

## - ጉዳያቸው በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ እንዲታይ ይደረጋል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በወንጀል ተጠርጥረው ክስ ቀርቦባቸው የነበሩ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ሲቪል እና ወታደራዊ አመራሮች ክስ መቋረጡን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር አስታወቀ። ክስ ቀርቦባቸው የነበሩ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ሲቪል እና ወታደራዊ አመራሮች ጉዳያቸው በቀጣይ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ እንዲታይ ይደረጋል ተብሏል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የክስ መነሳትን አስመልክቶ በማኅበራዊ ትስስር ገፁ በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በወንጀል ተጠርጥረው ክስ ቀርቦባቸው የነበሩ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ሲቪል እና ወታደራዊ አመራሮች ክስ ተቋርጧል።

በፌዴራል መንግሥት እና በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መሃከል በተፈረመው የሰላም ስምምነት መሠረት ከግጭቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ ወንጀሎች ተጠያቂነት በተመለከተ ያለውን ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ሊታዩ እንደሚገባ ስምምነት ላይ ተደርሷል ያለው መግለጫው፤ ስለሆነም በወንጀል ተጠርጥረው ክስ ቀርቦባቸው የነበሩ የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ሲቪል እና ወታደራዊ አመራሮችን ክስ በማቋረጥ ጉዳያቸው በቀጣይ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ እንዲታይ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብሏል።

ስለዚህ በተገለፀው አግባብ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀርቦ በክርክር ሂደት ላይ ይገኙ የነበሩ የወንጀል ክሶች በአዋጅ 943/2008 አንቀጽ 6 (3) (ሠ) መሠረት የተነሱ መሆኑን እናሳውቃለን ብሏል በመግለጫው።

ሁለቱ ኃይሎች በደቡብ አፍሪካ የሰላም ስምምነት ማድረጋቸው እና በኬንያ ናይሮቢም በአተገባበሩ ላይ ተወያይተው መስማማታቸውና በቅርቡም የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር መዋቀሩ ይታወሳል።

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

# በበጋ የምርት ዘመን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ክረምት በርካታ ኩንታል ስንዴ ተገኝቷል። በተያዘው ዓመት የበጋ ወቅት ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በምርት ተሸፍኗል። በዚህም በዘንድሮ የበጋ ምርት ዘመን ከ40 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይገኛል።

እንደ ዶክተር ዐቢይ ማብራሪያ፤ ባለፉት 50 እና 60 ዓመታት ስንዴን ከውጭ አገር በማስገባት የምትታወቅ አገር ለመጀመሪያ ጊዜ በያዝነው ዓመት ለስንዴ ግዥ አንድም ዶላር አላወጣችም ይህ ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል።

ሆኖም በአዲስ አበባ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ የዋጋ ንረት ማጋጠሙን ጠቁመው፣ የዋጋ ንረቱ የተፈጠረው የምርት እጥረት ሰላለ ሳይሆን ሆን ተብሎ በሚደረጉ የምርት መደበቅና ገና ለገና ወደፊት ሊወደድ ይችላል በሚል እሳቤ ምርትን የማከማቸት ችግር እንደሆነ ተናግረዋል። እጥረቱን ለመፍታትም ምርት ወደ መዲናዋ እንዲገባ እየተደረገ መሆኑንና ይህም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አብራርተዋል።

በርካታ አገራት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የስንዴ ምርት እየተመረተ መሆኑን እየመሰከሩ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የስንዴ ማምረት ሥራው ሲጀመር «ጦርነት ላይ እያለን የስንዴ ምርት ምን ያደርጋል? አያስፈልግም ማለት፣ ምርቱ ሲመጣና ለውጭ ገበያ ስናቀርብ የሌላትን አበደረች የሚል ብሂል እየመጣ ነው» ይህ ደግሞ ተገቢ አይደለም ብለዋል።

ሆኖም ይህ የሚያኮራ ምርት ለምን ድሃው ማህበረሰብ ጋር አልደረሰም የሚለው ትክክል ነው፤ ተረባርበን የዋጋ ግሽበቱን ለመቀነስ መሥራት አስፈላጊ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ምርቱን በማምረት ትልቅ ድል ተሠርቷል። ነገር ግን የንግድ ሥርዓቱ መስተካከል አለበት። ኬላ በመዘጋትና ፍተሻ በማብዛት የሚፈጠሩ ችግሮችን ለማስተካከል ይሠራል።

ሩሲያ ስንዴ ወደ ውጭ ገበያ ስትልክ በአገር ውስጥ ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩን ያስታወሱት ዶክተር ዐቢይ፤ ከውጭ ገበያ ወደ አገሯ ታስገባ ነበር። ከጥገኝነት ተላቃ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ስትጀምር ልክ እንደ ኢትዮጵያ በአገር ውስጥ ከፍተኛ የምርት ፍላጎት ነበር።

በተመሳሳይ በቀጣይ ሁለትና ሦስት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ የስንዴ ምርት እያደገና አስተማማኝ በሆነ መንገድ ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ለሽያጭም በቂ የሆነ ምርት ይመረታል። ስንዴ ማምረትን ሰው እየተላመደው በመሆኑ፣ ማሽኖች እየበዙና በኩታገጠም የሚታረስ መሬት እየበዛ በመምጣቱ ምርቱ እየጨመረ እንደሚሄድ ገልጸዋል።

ምርት የሚከዝኑ አካላት ምርቶችን በመከዘን ፈንታ የገበያ እጥረት እንዳይኖር ከስር ከስር መሸጥ አስፈላጊ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በወቅቱ መሸጥ ካልተቻለ መከዘን ኪሳራ የሚያስከትል ነው ሲሉ አሳስበዋል። አዲሱ ምርት ሳይመጣ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይገባልም ብለዋል።

በየቤቱ ያለው ምርት ወደ ገበያ እንዲወጣና ኑሮን እንዲያረጋጋ ከመንግሥትና ከሕዝብ ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚጠይቅም አያይዘው ገልጸዋል።



# ርዕሰ አንቀፅ

## ስሰላም ውድ ዋጋ ስመክፈል ፋይዳውን በሚገባ መገንዘብን ይጠይቃል!

የሰላም ጉዳይ ቀልሎ የሚታያቸው አካላት ስለሰላም የሚከፈሉ ከፍ ያሉ ዋጋዎችን አሳንሰው ቢመለከቱ ወይም ትርጉም ባይሰጧቸው ብዙም የሚያስገርም የሚያነጋግር አይሆንም። ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት መሆኑን ተገንዝበው የሚጠይቀውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል የተዘጋጁና የሚከፍሉ ግን በሁለንተናዊ መልኩ የትውልዶች ባለውለታ የመሆናቸው እውነታ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

በተለይም ሀገርና ሕዝብ መስቀለኛ በሆነ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ በሚገኙባቸው ወቅቶች የሰላም ሀዋሪያ የሆኑ፣ ስለ ሰላም አበክረው የሚሰሩና የሚሰብኩ እንዲሁም ለዚህም ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጁ ኃይሎች ሀገርና ሕዝብን በመታደግ ለአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ጅማሬ በር ከፋች የመሆናቸው እውነታ በብዙ ሀገራት ታሪክ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ነው።

ይህም ሆኖ ሕዝብ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች አሮጌ አስተሳሰቦች እና የእነርሱ መገለጫ የሆኑ ድርጊቶችን ተቃውሞ ንቅናቄ በሚፈጥርበት፤ ንቅናቄውም ፈጣን ለውጥ በሚሻበት ወቅት፤ ይህንን አጋጣሚ ለጥፋት ተልዕኮ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ኃይሎች፤ ግጭቶችን እንደ አንድ የትግል ስትራቴጂ አድርገው መጠቀማቸው የተለመደ ነው።

በአንድ በኩል የሕዝቡን የለውጥ ፍላጎት ተረድቶ ፍላጎቱን ተጨባጭ ለማድረግ የሚንቀሳቀሰውን የለውጥ ኃይል ፋታ በመንሳት ሕዝቡ በለውጥ ኃይሉ ላይ የነበረውን እምነት እንዲያጣ ለማድረግ፤ በሌላ በኩል የለውጥ ኃይሉ ራሱ ከተነሳበት የለውጥ አስተሳሰብ አፈንግጦ ባልተገባ መንገድ እንዲሄድ፤ በዚህም አጠቃላይ ለውጡ ትርጉም አልባ እንዲሆን ግጭትን የትግል ስትራቴጂ አድርገው ይሰራሉ።

ባለፉት አምስት ዓመታት በሀገራችን በተጨባጭ የሆነውም ይሄ ነው። ሕዝባችን ብዙ ዋጋ ከፍሎ እውን ያደረገውን ለውጥና ለውጡን የሚመራውን ኃይል በየአካባቢው በተቀናጀና በተናበበ መልኩ በተፈጠሩ ግጭቶች፤ ግጭቶቹ በሚፈጥሩት ሞት ፣ መፈናቀልና የንብረት ውድመቶች ተስፋ በማስቆረጥ "ለውጥ ድሮ ቀረ " ወደሚል ትርክት ለመመለስ ብዙ ርቀት ተሄዷል።

ሰላምና የሰላም ጉዳይን በየትኛውም መልኩ የትግል ስትራቴጂ ማድረግ የማይችሉና ተፈጥሯዊ ማንነታቸው የማይፈቅድላቸው አንዳንድ ኃይሎች ስለሰላም የሚከፈል ዋጋ የቱን ያህል ውድ መሆኑን፣ ይህንን ዋጋ ለመክፈል ከፍ ያለ ስብዕና እንደሚጠይቅ መረዳት ሲያቅታቸው ይታያል።

ከሰላም የሚገኙ ዘርፈ ብዙ ፍሬዎች ሀገርን እንደሀገር ወደ ቀጣይ ያደገ የታሪክ ምዕራፍ የሚያሻግሩ ዋነኛ አቅሞች መሆናቸውን፤ ለእነርሱም ሆነ ለልጆቻቸው፣ ለልጅ ልጆቻቸው የተሻለች ሀገር በመፍጠር ሂደት ውስጥ ሰላም አልፋና ኦሜጋ መሆኑን ለመቀበልና ለሰላም ተገቢውን ትርጉም ለመስጠት የተዘጋጀ አዕምሮ የላቸውም። ግጭት ግጭትን እየወለደ እነሱንና የእነሱ የሆነውን ጭምር እንደሚበላ ለአፍታ ለማሰብም ፍቃደኛ አይደሉም።

በእነርሱ የተዛባ አስተሳሰብ ዋጋ እየከፈለ ስላለው ዜጋም ሆነ እየወደመ ስላለው የሕዝብ ሀብት የሚያስጨንቃቸው አይደሉም፤ ከዚህ ይልቅ ግጭት የትግል ስትራቴጂያቸው ከማድረጋቸው አንጻር፤ የዜጎች ሞትም ሆነ የሀገር ሀብት ውድመት እንደ ስኬት የሚቆጥሩ ናቸው። ለዚህም ነው በሚፈጥሯቸው ግጭቶች ሰለባ የሚሆኑ ዜጎችን የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ለማድረግ የሚተጉት።

መንግሥት ዜጎችን ለሞትና መፈናቀል የዳረጉ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለማስቆም እያደረገ ያለውን ጥረት ከማንቋሸሽ ጀምሮ ያልተገባ ትርጉም በመስጠት፤ ግጭቶች ዘላቂ ሆነው እንዲቀጥሉ ባላቸው አቅም ሁሉ ከፍ ባለ ድምጽ የሚጮሁትም ከዚህ ባህሪያቸው በመነጨ ነው።

መንግሥት በሀገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን ያለበትን የሕግና የሞራል ሃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በድርድር ለመፍታት እየሄደበት ያለው መንገድ አንድም ሰላም ከሁሉም በላይ የሕዝባችን ጥያቄ በመሆኑ፤ ከዚህም ባለፈ የሕዝባችን የመልማት መሻት /ብልጽግና/ ስኬታማ የሚሆነው ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት የመፍታት የፖለቲካ ባህልን ስናዳብርና ዘላቂ ሰላም ስናረጋግጥ መሆኑን ከመረዳት ነው። ይህ ደግሞ ሀገርን ለማጽናት ከሚሰራ አመራርና ሀገሩን ከሚወድ ሕዝብ የሚጠበቅ ቀና መንገድ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሽግግር ፍትህ ሂደት ተሞክሮ በኢትዮጵያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት በሽግግር ሁኔታ ውስጥ ብታልፍም በተሟላ መልኩ የሽግግር ፍትህ አላባዎች ተተግብረው አያውቁም፡፡ በነዚህ የሽግግር ሂደቶች ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ በደሎች እና ጭቆናዎችን መንስኤ፣ ምንነት፣ አይነት እና የጉዳት መጠን በበቂ መንገድ በማጣራት፣ እውነትን በማውጣት እና እውቅና በመስጠት በተጠያቂነት፣ በይቅርታ እና በእርቅ ላይ የተመሰረተ የተሟላ ሂደት አልተከናወነም።

የደርግ መንግሥት የአፄ ኃይለስላሴን መንግሥት ከሥልጣን ካስወገደ በኋላ በንጉሱ ሥርዓት ዘመን መጠነ ሰፊ በደል ፈፅመዋል፣ አለአግባብ በልጽገዋል እና ለወሎው ረሃብ እልቂት ተጠያቂ ናቸው ያላቸውን መኳንንቶች፣ መሳፍንቶች፣ ሚኒስትሮች እና ሌሎች ባለሥልጣናትን አስሯል። የነዚህን ባልሥጣናት ጉዳይ እያጣራ ለፍርድ የሚያቀርብ አጣሪ ኮሚሽንም ተቋቁሞ ነበር፡፡ አጣሪ ኮሚሽኑ ምርመራውን ማካሄድ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም - ምርመራውን ከማጠናቀቁ በፊት ደርግ ከ50 በላይ በሚሆኑት ባለሥልጣናት ላይ የሞት ፍርድ ውሳኔ በማስተላለፍ እርምጃ እንዲወሰድ አድርጓል፡፡

በ1983 ዓ.ም. ኢህአዴግ በትረ-መንግሥቱን በመቆጣጠር የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የመሰረተ ሲሆን፤ በደርግ አስተዳደር ዘመን ለተፈጸሙ ጥሰቶች ምላሽ ለመስጠት የወንጀል ክስ መመስረትን እንደ ዋነኛ መንገድ ተጠቅሟል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 22/1985 መሰረት ተጠሪነቱ በቀጥታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሆነ ልዩ የዓቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት የተቋቋመ ሲሆን፣ በስሩም ከ400 በላይ ሰራተኞች ነበሩት፡፡ የጽህፈት ቤቱ ዋና ስራም የደርግ ባለሥልጣናት የፈጸሟቸውን ወንጀሎች መመርመር፣ ክስ መመስረት እና ማስቀጣት ነበር፡፡

በዚህም መሰረት በተለያዩ ሰዎች ላይ ምርመራዎችን በማጣራት፣ በመደበኛው ፍርድ ቤት ክስ በመመስረት እና በመከራከር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ጨምሮ በበርካታ ተጠርጣሪዎች ላይ የቅጣት ውሳኔ እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ በዚህ ሂደት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎችን የማደራጀት እና ክስ የመመስረት ስራው ራሱን በቻለ ተቋም እንዲሰራ መደረጉ በጥንካሬ ሊወሰድ የሚገባው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በቀጣይ ዓመታት አዲስ ሕገ-መንግሥት የማውጣት፣ ዴሞክራሲያ ተቋማትን - ማለትም የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን - የማቋቋም ስራ ተሰርቷል። በዚህ ወቅት የነበረውን የፍትህ ሂደት ከሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎች አንፃር ስንመለከተው የሚከተሉት ጉድለቶች እንደነበሩበት መረዳት ይቻላል፡-

- የፍትህ ሂደቱ መጠነ-ሰፊ የሆነ የወንጀል ክስ በማቅረብ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጉ እና በደርግ ጊዜ የተፈጸመውን ግፍና በደል በበቂ ሁኔታ ለመሸፈንና ለመፍታት የሚያስችሉ እንደ ይቅርታ፣ እርቅ እና እውነትን ማፈላለግ ያሉ ስልቶችን አለመጠቀሙ፤

- በደርግ መንግሥት የሥልጣን ዘመን በሌሎች አካላት የተፈፀሙ በደሎች እንደነበሩ ቢታወቅም ፤ የክስ ሂደቱ በደርግ ባለሥልጣናት ላይ ብቻ ማተኮሩ ፣ በተለይም በሌሎች ሲቪል እና ታጣቂ ቡድኖች ተፈጽመዋል የተባሉ ወንጀሎችን አለማየቱ፤ የፍትህ ሂደቱን የአሸናፊዎች ፍትህ ተምሳሌት እንዲሆን ማድረጉ፤

- በፍትህ ሂደቱ የነበረው የተጎጂዎች ተሳትፎ ማስረጃ በማቅረብ ላይ ብቻ መገደቡ፣ እንዲሁም የክሱ ሂደትም ቢሆን ከፍትሐ ብሔር ክስ ጋር ያልተጣመረ እና ማካካሻ የማግኘት መብትን ያስከበረ አለመሆኑ፤

- የድርጊቱ ሰለባዎች እና ተጎጂዎች በቂ ማካካሻ እንዲያገኙ አለማድረጉ ከሚጠቀሱ ክፍተቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በ2010 ዓ.ም. በሀገራችን የተፈጠረውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ ፣መንግሥት ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ ቁርሾዎች እና በደሎች በእውነት በእርቅ እና በፍትህ ላይ ተመስርቶ ለመፍታት እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መንገዱን ለማመቻቸት - በርካታ የሽግግር ፍትህ እርምጃዎችን ወስዷል። ለደረሱ በደሎች እንደመንግሥት በይፋ ይቅርታ የመጠየቅ፣ የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን የማቋቋም፣ ክስ፣ ምህረት እና ለሽግግር ፍትህ ሂደት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሕግ እና የተቋማት ማሻሻያ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

ይሁንና የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተሟላ እና ወጥ በሆነ መልኩ ተቀናጅተው የሚተገበሩበት የፖሊሲ አቅጣጫ ባለመኖሩ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ያለው መስተጋብርም በግልፅ ባለመደንገጉ፣ እንዲሁም የተወሰዱት እርምጃዎች የየራሳቸው ጉድለቶች ስለነበሩባቸው የሽግግር ፍትህ ሂደት ዓላማን ማሳካት አልተቻለም፡፡ ከተደረጉት ጥረቶች እና ከነበሩ ጉድለቶች መካከል የሚከተሉትን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል፡-

### የወንጀል ክሶችን በሚመለከት፤

ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ከባድ ሙስና እና/ወይም ሌሎች ከፍተኛ የሕዝብ ንብረት ምዝበራ ድርጊቶችን በተመለከተ በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ክስ ቀርቦ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የታየ /በመታየት ላይ ያለ ቢሆንም ይህ ሂደት ከሽግግር ፍትህ ሂደት ዘዴዎች እና አላባዎች አንፃር የሚከተሉት ዋና ዋና ጉድለቶች ያሉት መሆኑ ተለይቷል፡፡

- ክሶቹ በኢህአዴግ ዘመነ-መንግሥት በደረሱ ጠቅላላ ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ያተኮሩ አለመሆናቸው፣ ክስ ሊቀርብባቸው የሚገቡት ጉዳዮችን በሙሉ ያላካተተና በእጅጉ አናሳ የበዳይ ወሰን ያለው መሆኑ፤

- በአመዛኙ ክሶች የቀረቡት ሊከሰሱ ከሚገባቸው መካከል ማማረጥ በሚመስል መልኩ መሆኑ፤

- ረዥም የፍርድ ሂደት መኖሩ፤ አብዛኛዎቹ ጉዳዮች አሁንም ድረስ ውሳኔ አለማግኘታቸው፤

- የጉዳት ሰለባዎች እና የተጎጂዎች ማካካሻ የማግኘት መብትን ባስከበረ መልኩ የሚካሔድ የክስ ሥርዓት አለመሆኑ፣ ይህም በተጎጂዎችና በህብረተሰቡ የፍትህ መጓደል ስሜት ከመፍጠሩም ባሻገር ፤ለእርቅ አስተዋፅኦ አድርጓል ለማለት የማያስችል ሂደት መሆኑ፤

- የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አክብሮ በማስከበር፣ እንዲሁም ያለፉ ጥፋቶች እንዳይደገሙ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ እንደ ፖሊስ፤ ዐቃቤ ሕግ፤ ፍርድ ቤቶች እና በሌሎች የፍትህና ዴሞክራሲ ተቋማት ላይ ከተወሰነ የአመራር ለውጥ በስተቀር - ይህ ነው የሚባል በማጣራት እና በልየታ ላይ የተመሰረተ የሽግግር ስልትን (vetting) የተገበረ ለውጥ አለመከናወኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### ምህረትን በሚመለከት፤

የምህረት አሰጣጥና አፈፃጸም ሥርዓት ወጥነት ስላልነበረው ይህን ለማስተካከል የምህረት አሰጣጥ እና አፈጻጸም ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1089/2010 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ይህን አዋጅ መሰረት አድርጎ በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ ለተሳተፉ ሰዎች ምህረት ለመስጠት የሚያስችል አዋጅ ቁጥር 1096/2010 ወጥቷል።

ዓላማውም በነበረው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ምክንያት በወንጀል የተሳተፉ ሰዎችን ምህረት በመስጠት ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን፣ ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር እና ይቅር መባባልን ለማበረታታት፣ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት ፣ በተለይም ፖለቲካዊ መብታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ በመንቀሳቀሳቸው የወንጀል ተጠያቂነት ስጋት ላደረባቸው ኢትዮጵያውያንና

# ነፃ ሃሳብ

## የሽግግር ፍትህ ሂደት...

ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ምህረት በመስጠት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት በማስፈለጉ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ተገልጿል። ይሁንና ይህ ሂደት ከሽግግር ፍትህ ሂደት ዘዴዎች እና አላባዎች አንፃር የሚከተሉት ጉድለቶች ነበሩት፡፡

- የምህረት አሰጣጥ ሂደቱ ወንጀል ፈፃሚ ተብለው በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ከመጠየቅ ውጪ ምንም አይነት ቅድመ-ሁኔታ ያላስቀመጠ መሆኑ፣ ይህም በሽግግር ፍትህ ሂደት የማይመከረውን አይነት ጠቅላላ ምህረት (blanket amnesty) የሰጠ መሆኑ፤

- የምህረት ሂደቱ ተጎጂዎችን ያላሳተፈ መሆኑ፣ በውስጡም ተጎጂዎችን የመካስ እና ይቅርታ የመጠየቅ ሥርዓቶች ያልተካተቱበት መሆኑ፤

- ሰላምና መረጋጋት ከማምጣት አንጻር ከታየ በአዋጁ ተጠቃሚ ሆነው ከእስር የተለቀቁ ሰዎች ባለፉት አራት ዓመታት በተከሰቱ ግጭቶች ውስጥ ተመልሰው መሳተፋቸው እና በቁጥጥር ስር መዋላቸው ሲታይ ከመፀፀት ጋር በተያያዘ የታለመውን ግብ ያላሳካ መሆኑ፤

- በምህረት ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ሰዎች በፌዴራል እና በክልል መዋቅሮች በተዘጋጁ ቢሮዎች በመቅረብ እና በማመልከት የምህረት ምስክር ወረቀት የሚወስዱበት ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም ፣አፈፃፀሙ ላይ ጠንከር ያለ ክትትል ባለመደረጉ - የምህረት አሰጣጥ እና አፈፃፀም ሥርዓቱ በአግባቡ አለመከናወኑ፤የምስክር ወረቀት ያልያዙ ሰዎችም በማናለብኝነት ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀላቸው፣ ይህም የመንግሥትን ሕግ የማስከበር ብቃት ጥያቄ ውስጥ ያስገባው መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ

ለሀገራችን የመጀመሪያ የሆነው የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 1102/2011 ተቋቁሞ የነበረ ሲሆን፤ ኮሚሽኑም በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት እና በተደጋጋሚ የተፈጸሙ ጉልህ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን፣ በደሎችን፣ ቁርሾዎችን እና ዝንፈቶችን በበቂ ደረጃ ለይቶና አጣርቶ እውቅና በመስጠት  በእውነት፣ እርቅ እና ፍትህ ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ሰላም እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ሥልጣን እና ሃላፊነት ተሰጥቶታል።

ይሁንና ተቋሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ የዝግጅት ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቶ ዋና ተግባሩን መፈፀም ሳይጀምር እና ተጨባጭ ውጤት ሳያስገኝ  የተሰጠው የሶስት ዓመት የስራ ዘመን የካቲት 2014 ዓ.ም በማብቃቱ እንዲፈርስ ተደርጓል። ኮሚሽኑ ከሽግግር ፍትህ አንፃር የተጣለበትን ዓላማ ማሳካት ላለመቻሉ የሚከተሉትን ምክንያቶች በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

- የኮሚሽኑ የምስረታ ሂደት ትርጉም ያለው እና ሀገር-አቀፍ የሕዝብ ምክክር ያልተደረገበት መሆኑ፣ በረቂቁ ላይ ከሚመለከታቸው አካላትና ባለሙያዎች ጋር ምክክር አለመደረጉና ግብዓት አለመወሰዱ፣

- ለኮሚሽኑ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ግልፅነት የጎደለውና ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑ፣ ተግባርና ኃላፊነቱ ከሌሎች የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ጋር የነበረው መስተጋብር እና የመመጋገብ ግንኙነት በግልፅ አለመቀመጡ፣ ኮሚሽኑ ይቅርታ እና ምህረት እንዲሰጥ ሥልጣን ያልተሰጠው መሆኑ፤

- የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ሲመረጡ እና ሲሾሙ ቀጥተኛ የሕዝብ ጥቆማ፣ ውይይት እና ተሳትፎ ያልነበረ መሆኑ፤ ይህም በኮሚሽኑ ቅቡልነት ላይ አሉታዊ አስተዋጽኦ ማድረጉ፤

- በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበሩ እንዲሁም ገለልተኝነታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ - በዳይ ወይም ተበዳይ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ግለሰቦች ኮሚሽነር ሆነው መሾማቸው፤

- ለዚህ ከፍተኛ ሃላፊነት የሚሰየሙ ኮሚሽነሮች የሙሉ ሰአት ሰራተኞች አለመሆናቸው፣ ቁጥራቸውም ከተለመደው እጅግ የበዛ (41 የሚጠጋ) መሆኑ፣

- ኮሚሽኑ የሚያጣራቸው ያለፉ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከየትኛው ጊዜ እንደሚጀመር አለመቀመጡ፣

- ተቋሙ ከሚችለው በላይ ሃላፊነት የተሰጠው መሆኑ (ለምሳሌ አሁናዊ ግጭት መፍታት ላይ የሚሰሩ እና እንዲሰሩ ሃላፊነት የተሰጣቸው መንግሥታዊ ተቋማት እያሉ ፣ይህንን ተግባር ጊዜያዊ ለሆነው የእርቀ-ሰላም ኮሚሽን ተጨማሪ ተግባር እንዲሆን መደረጉ፣ ሀገራዊ ምክክር የማድረግ ተጨማሪ ተግባር የተሰጠው መሆኑ፣

- እንደ እርቀ-ሰላም ያሉ ኮሚሽኖች ግጭት መፍታት እና ሀገራዊ ምክክርን ማካሄድ ዋና ተግባራቸው እንዲያደርጉ በማይመከርበት ሁኔታ ይህ መፈፀሙ።

> **የሀገሪቱን አሁናዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ፣ ያለፈውን በአግባቡ የሚያስተናግድ፣ ለነገም መሰረት ለመጣል የሚያስችል፣ በዓለም-አቀፍ እና ሀገራዊ ልምዶች የተቀመረ፣ እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ አጀንዳዎችን ይዘውና ነፍጥ አንግበው የሚታገሉ ቡድኖችን ትጥቅ አስፈትቶ ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ የሚያደርግ - የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር የግድ ይላል፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ ሀገሪቱ ካሉባት ውስብስብ ችግሮች አዙሪት እንድትወጣ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል**

በአጠቃላይ ሀገራችን በነበሩት የሽግግር አጋጣሚዎች-የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎችን ለማሳካትም ሆነ ፍትህን ለማረጋገጥ ውስን ሙከራዎች እንደነበሩና በዚህም የተገኙ ልምዶችና ውጤቶች እንዳሉ መመልከት ይቻላል። ይሁንና ከ2010 ዓ.ም በኋላ የተከናወኑትን ጨምሮ  በኢትዮጵያ የተደረጉ የሽግግር ፍትህ ሙከራዎች ያልተሟሉ እና በቂ ባልሆኑ ሂደቶች የተተገበሩ እንደነበሩ ተስተውሏል።

በተሟላ መልኩ - የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎችን እና ዘዴዎችን አካትተው፣ በተቀናጀ ሁኔታ ባለመተግበራቸውም - ስኬታማ መሆን አልቻሉም፡፡

በመሆኑም ካለፈው አስከፊ ሁኔታ በመማር ወደ ፊት ለመራመድ - የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የሚፈጥሯቸውን አጋጣሚዎች እንዳንጠቀም ምክንያት ሆነዋል። ይህም በራሱ እስካሁን ድረስ ለቀጠለው ግጭት፣ የእርስ በእርስ ጦርነት እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መንስኤ የሆኑ በርካታ ጉዳዮች ሳይፈቱ እንዲቀጥሉ አስተዋፅኦ አድርጓል።

### በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በ2010 ዓ.ም የመጣውን ለውጥ ጨምሮ - በኢትዮጵያ የተሞከሩት የሽግግር ፍትህ አላባዎች የታለመላቸውን ዓላማ ማሳካት አልቻሉም፡፡ ስለሆነም በተሟላ እና በተቀናጀ መልኩ የሚዘረጋ፣ አሳታፊ የሆነ፣ ተጎጂዎችን ማእከል ያደረገ፣ የዓለም -አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆችንና ድንጋጌዎችን ያከበረ፣ በሌሎች ሀገራት እና በሀገራችን ከነበሩ ልምዶች ትምህርት የሚወስድ፣ የሀገራችንን ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ አውድ ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ የሽግግር ፍትህ ሂደት በመቀመር እና በግልፅ የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲመራ በማስቻል ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ምክንያቶች በማሳያነት ማንሳት ይቻላል፡-

ሀ) የሀገራዊ አውዱ ሁኔታ የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ሂደትን መተግበር አስፈላጊ እንደሆነ የሚያመላክት መሆኑ፤

በኢትዮጵያ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ስልታዊና መጠነ-ሰፊ በሆነ ሁኔታ ሲፈጸሙ የነበረ ስለመሆኑ በርካታ ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡ ከ 2010 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ የፍትህ ማሻሻያ ስራዎች ቢሰሩም የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ አለመረጋጋት፣ ግጭቶች እና የእርስ-በርስ ጦርነት በመቀጠሉ አሁንም ዜጎች ለሞት፣ ለስደትና ለንብረት ውድመት እየተጋለጡ ይገኛሉ።

ከዚህ የጥፋት አዙሪት እንዳንወጣ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል - በሀገራችን የነበሩ የተደራረቡ በደሎች፣ የመብት ጥሰቶች፣ የተዛነፉ የታሪክ አረዳዶች፣ ለእነዚህ ጥሰቶች የተሰጡ ምላሾች ምሉዕ አለመሆን፣ በዜጎች ላይ ለተፈፀሙ ጥሰቶች ፍትህ አለማግኘት፣ ተጎጂዎች አለመካሳቸው፣ እና ሀገራዊ እርቅ አለመከናወኑ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የአጥፊዎች እና የተጎጂዎች ብዛት፣ የበደሎች መደራረብ፣  እና የጥፋቶች ማህበረሰባዊ ቅርፅ መያዝ ሕዝቡ ለፍትህ ተቋማት ካለው ያነሰ ቅቡልነት ጋር ተዳምሮ

- በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት እና አካሄድ ለሁኔታዎች ፍትህ መስጠትም ሆነ ይቅርታና እርቅ ማከናወን እንዳይቻል አድርጎታል፡፡

ስለሆነም የሀገሪቱን አሁናዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ፣ ያለፈውን በአግባቡ የሚያስተናግድ፣ ለነገም መሰረት ለመጣል የሚያስችል፣ በዓለም-አቀፍ እና ሀገራዊ ልምዶች የተቀመረ፣ እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ አጀንዳዎችን ይዘውና ነፍጥ አንግበው የሚታገሉ ቡድኖችን ትጥቅ አስፈትቶ ከማህበረሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ የሚያደርግ - የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር የግድ ይላል። ይህ አይነቱ አካሄድ ሀገሪቱ ካሉባት ውስብስብ ችግሮች አዙሪት እንድትወጣ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ለ) የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት ለሀገረ-መንግሥቱ ግንባታ እና ቀጣይነት የሚኖረው ሚና ከፍ ያለ መሆኑ፣ በሀገራችን ከነበረው የጥፋት አዙሪት ለመውጣት እና ለተፈጠሩ ጥሰቶች አግባብ ያለው ምላሽ ለመስጠት በእውነት፣ በፍትህ፣ በሰላም እና በእርቅ ላይ በመመስረት ማህበራዊ ግንኙነቶችን ማደስ እጅግ አስፈላጊ ነው። በታሪክ ኢትዮጵያ እውነተኛ የእርቅ ሂደትን አድርጋ የምታውቅበት ወቅት ወይም አጋጣሚ የለም፡፡

ይልቁንም በአንዳንድ ዘመናት ሥልጣን ላይ የነበሩ መንግሥታት የያዙት አቋም "የተጣላ የለም፤ እርቅ አያስፈልገንም" የሚል ይዘት የነበረው እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት - በሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና ቁርሾዎች አግባብነት ባለው መልኩ ሳይፈቱ እየተንከባለሉ እዚህ ዘመን ላይ ደርሰዋል፡፡

ስለሆነም ያለፉ በደሎችን አንስቶ መወያየት ፈታኝ ቢሆንም -ይቅር መባባልና እርቅ እንዲኖር ማድረግ ለሀገረመንግሥቱ ግንባታ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። በሀገሪቱ የነበሩና የቀጠሉ ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ካልተበጀላቸው  ታሪካዊ ኢ-ፍትሃዊነትን የሚያሳዩ ተፃራሪ ትረካዎች ሕብረተሰቡን በተለያየ መንገድ ማቁሰላቸውን እንዲቀጥሉ ያደርጋል። በመሆኑም ሀገሪቱ የተከፋፈለውን ሕዝብ ለማቀራረብ፣ የሻከረውን ግንኙነት ለመጠገን፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና እርቅ ለመፍጠር የሽግግር ፍትህ ዘዴዎችን መጠቀም እንደ አማራጭ መውሰድ ይኖርባታል፡፡ በዚህ ሂደት ላለፈው ቁስል እውቅና ለመስጠት፣ የሰውን ክብር ለመመለስ፣ ለጋራ ዳግም ውህደት እና ለሀገር ግንባታ የሽግግር ፍትህ የሚኖረው ሚና እጅግ ወሳኝ ነው፡፡

ሐ) የተሳካ የሽግግር ፍትህ ሂደት ሳይተገበር የዴሞክራሲ ሽግግርም ሆነ ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ የማይቻል መሆኑ፡፡

በተለያዩ ሀገሮች እንደታየው ያለፉ በደሎችን እና ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በአግባቡ ሳይፈቱ፣ ሙሉ እውነትን ሳያወጡ፣ ተጠያቂነትን ሳያሰፍኑ፣ እና እውቅና ሳይሰጡ  በእርቅ፣ በሰላም እና በፍትህ ላይ የተመሰረተ የተሳካ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ማድረግ አዳጋች ነው።

በዚህም ምክንያት በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙ ጉልህ የመብት ጥሰቶች እና ቁርሾዎች አግባብነት ባለው መልኩ ሳይፈቱ ሲንከባለሉ የመጡ እንደመሆኑ መጠን በደሎቹ እንዲሽሩ፣ ቁርሾዎች እንዲጠገኑ፣ ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር እንዲሳካ፣ እንዲሁም ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ እንዲቻል - የተሟላ የሽግግር ፍትህ ሂደት መተግበር ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

መ) የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መተግበር ለሰብአዊ መብት መከበር እና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ የማይተካ መሆኑ፤

በሀገራችን ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት የተፈፀመ ቢሆንም- ሁሉንም አጥፊዎች እንደየጥፋታቸው ያለምንም ወጣ ገባነት ተጠያቂ የሚያደርግ ሥርዓት አለመኖሩ ጥሰቶቹ ተደጋግመው ለመከሰታቸው አንዱ ምክንያት ሆኗል፡፡ እነዚህ ጥሰቶች በአብዛኛው የተፈፀሙት ምንም አይነት የፖለቲካ ተሳትፎ በሌላቸው፣ ስለነገሩም ምንም ግንዛቤ ባልያዙ ኢትዮጵያውያን ላይ ነው። ድርጊቶቹ እንዳይፈፀሙ የመቆጣጠር ወይም የመከላከል ኃላፊነት ያለባቸው የመንግሥት ሃላፊዎች እና የማህበረሰብ ልሂቃኖችም  ነገሮች እንዲባባሱ ጉልህ አስተዋፅኦ ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡

እነዚህ ድርጊቶች ተደጋግመው ስለሚፈፀሙ እና ከተፈፀሙ በኋላም ምርመራው ይሁን የክስ ሂደቱ ተጎጂዎችን ያላማከለ እና በህብረተሰቡም እምነት የተጣለበት ባለመሆኑ - በሂደት ሕዝቡ በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ያለው እምነት አናሳ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

ስለሆነም ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ - ተቀባይነት ያለው የክስ ሂደትን እንዲኖር፣ ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተገቢ ትኩረት እንዲሰጥ፣ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲጠናከር፣ ተጎጂዎችን ማእከል ያደረገ የይቅርታ፣ እርቅ እና ማካካሻ ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ - ለሰብአዊ መብቶች ባህል መዳበር እና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ መሰረት ይጥላል።

**ምንጭ /ኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች በሚል ጥር 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ለመሰብሰብ በተዘጋጀ መድረክ ለውይይት ከቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ የተወሰደ /**

# ‘ጢግ ጉላ’ - የሃድያ ሕዝብ ከበደል የመንፃት ሥርዓት

**ማህሌት አብዱል**



በኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪካዊና ባህላዊ ሥርዓት ካላቸው ማህበረሰቦች መካከል የሃድያ ሕዝብ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ሕዝብ የራሱ የሆነ ቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ሥነ-ጥበብ፣ ወግና፣ የኑሮ ዘይቤ ያለው ሲሆን በተለይም ማህበረሰቡን አስተሳስሮ ለዘመናት ያኖሩ፤ ከትውልድ ትውልድ የተሻገሩ ፤ ለሀገርም አንድነት ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው በህላዊ ዕሴቶች ባለቤት ነው፡፡ ከእነዚህ ባህላዊ ሥርዓቶች መካከል ‘ጢግ-ጉላ’ የተሰኘው የጥል፣ የበቀልና የፀፀት ስሜትን ወደ ሰላማዊና ጤናማ ግኑኙነት የመመለስ ሥርዓት ዋነኛው ነው፡፡ የዛሬው ሀገርኛ አምዳችችንም በዚህ ሥርዓት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን የሃድያ ባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁርንም አነጋግሮ እንደሚከተለው ይዞላችሁ ቀርቧል፡፡

ጥናት አድራጊው ምሁር መምህር ግርማ ሱልዶሎ የሚባሉ የብሔረሰቡ ተወላጅ ሲሆኑ በዞኑ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመምህርነትና በርዕሰ መምህርነት ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል፡፡ መምህር ግርማ እንደሚሉት፤ ጢግ- ጉላ በሃድያ ሕዝብ ከሚፈፀሙ ባህላዊ አስተዳደር ሥርዓቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በተለይም በማህበረሰቡ በግጭት አፈታት ሥርዓት ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ የሚገኝና ግጭትን በማርገብ፤ ጠብን በማራቅ ጠንካራ ቤተሰባዊ ግኑኝነት እንዲፈጠር በማድረግ ረገድ ትልቅ ድርሻ ያለው ባህላዊ ክዋኔ ነው፡፡

በሀድያ ማህበረሰብ ዛሬም ድረስ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ይህ ‘ጢግ -ጉላ’ የተባለው የእርቅ ሥርዓት በተለይም አንድ ግድያ ከተፈፀመ በኋላ በቂም በቀል ሌላ ደም መፋሰስ እንዳይመጣ በማድረግና አካባቢውን በማረጋጋት በኩል አወንታዊ ሚና እየተጫወተ መሆኑን መምህሩ ያስረዳሉ፡፡ «ጢግ- ጉላ ሰዎች የግድያ ወንጀል ሲፈፅሙ ወደ ፍፁም ይቅርታ የማምጣት ሥርዓት የሚፈፀምበትና ዛሬም ድረስ ለትውልድ እየተላለፈ ያለ አስተዳደራዊ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ አስተዳራዊ ሥርዓት ላይ በባህላዊ አስታዳደር ጉባኤ ከሚታዩ ጉዳዮች መካከል የሚጠቀስ ነው» ይላሉ፡፡

‘ጢግ-ጉላ’ የበቀል፣ የክፋት፤ የጥፋት፤ የበደል ስሜትን በማንፃት ቤተሰባዊ ሰላም፣ ጤና እና የአባትና የልጅ ፤ የወንድም እና የእህት ግኑኝነት የመፍጠር ሥርዓት መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡ «በቀል ፤ መገዳደል ፤ ማውደም፤ ማግለል የሌለበትና ፈፅሞ በፍቅር ላይ የተመሰረተ፤ ፍፁም ይቅርታን የያዘ የእርቅ፤ የማገናኘት፤ የማስተሳሰር ሥርዓት ነው» በማለት ይናገራሉ፡፡ በተለይም አንዴ ግድያ ከተፈፀመ በኋላ ያለተጨማሪ ደም መፋሰስ ጉዳዩ መቋጫ እንዲያገኝ የሚደረግበት ፍቱን የእርቅ ሂደት መሆኑንም ያመለክታሉ፡፡ ለጠፋ ሕይወት ሌላ ሕይወት ማጥፋት ሳያስከትል ያለበቀል በፍፁም ይቅርታ፤ በልባዊ ፍቅር፤ ቤተሰባዊ ውህደት ፈጥሮ የማስታረቅ ብልሃት ተብሎም በማህበረሰቡ ዘንድ የሚተረጎም መሆኑንም ያብራራሉ፡፡

ይህ ሥርዓት ሲፈፀም ብዙ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉ መሆኑን የጠቀሱት መምህር ግርማ፤ በዋናነት ሶስት ዘርፎች በተለየ መልኩ የሚታዩ መሆኑን፤ ከእነዚህም መካከል የሽማግሌዎች የአስተዳደር ጉባኤ አንዱ እንደሆነና ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ ጎሳና ብሔረሰብ አስታደደር የሚደርስ አምስት መዋቅር ያለው መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ይህ ሥርዓት ሲፈፀም የእነዚህ ዘርፎች መሪዎች በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን ወደ እርቅ የሚያመጡበት ሂደት መኖሩን ያነሳሉ፡፡

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ በ’ጢግ-ጉላ’ ሥርዓት የገደለውን ሰው ወደ ይቅርታ ለማምጣት፤ በጥፋቱ እንዲፀፀት እና የሟች ቤተሰብ ፍፁም ይቅርታ እንዲያደርግ፤ ይህንን ሥርዓት ማህበረሰቡ እየፀለየ፣ እየመረቀ ፤ እየባረከ የሚመራ አንጃንቾ ወይም ከሽማግሌዎች መሪ ይሰየማል። ይህ ሰው በጣም በእድሜ የገፋ ሊሆን የሚገባው ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ መመረቅ፤ መባረክ ይችላል ፤ ፀሎቱ ይሰማል ተብሎ የሚታመን መሆን ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በጣም ከፍተኛውን የዳኝነት ስፍራ የያዘ ‘ሂራጋኖ’ በመባል የሚታወቅ ሰው የመጨረሻውንና ትክክለኛውን ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

የሂራጋኖዎች ቁጥር በአጠቃላይ በዞን ደረጃ ከአራት የማይበልጥ መሆኑን መምህር ግርማ አመልክተው፤ ጉዳዩን እንዲያይ የተመረጠው ‘ሂራጋኖ’ የችግሩን ምንጭ ከስር መሰረቱ በማጣራት፤ መርምሮና ተንትኖ ምን መደረግ እንዳለበት የውሳኔ ሃሳብ ለሽማግሌዎቹ የሚሰጥ ቁልፍ ሰው መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡ የእነዚህ አካላት ሚና እጅግ ከፍተኛ መሆኑን አንስተው፤ በተለይም የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጡ በመሆኑ እውነተኛ እና ክልብ የሆነ ይቅርታ እንዲመጣ በማድረገድ ረገድ በህብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ አመኔታ የተሰጣቸው መሆኑንም ነው ያስገነዘቡት። «የሽማግሌ መሪዎቹ በገዳይና በሟች ቤተሰብ መሃል ጣልቃ ይገቡና ከእነሱ ከፍ ያለውን ደግሞ መሪ አድርገው ተሰባስበው የሟች አባት በር ላይ እየሄዱ ደጅ ይጠናሉ፤ እርቅ እንዲመጣ፤ ሰዎች እንዳይተላለቁ የማድረግም ስራ ይሰራሉ» ሲሉም ጥናት አድራጊው ያብራራሉ፡፡

እንደመምህር ግርማ ማብራሪያ፤ ነፍስ ከጠፋ በኋላ በመጀመሪያ የገዳዩ ቤተሰብ መዋቅር ውስጥ ያሉ ሽማግሌዎች ወደ ሟች ቤተሰብ ሽማግሌዎች ጋር በመሄድ ውይይት ያደርጋሉ፡፡ በመቀጠል ወደ ሟች ቤት ይሄዱና ወደ ክስ እንዳይኬድ በባህላዊ ሥርዓቱ ተፅእኖ ይፈጥራሉ። ሽማግሌዎች ጉዳዩን ይዘው የግድያውን መነሻና መሰረቱን እንዲያጣራና መፍትሔ እንዲሰጥ’ ሂራጋኖ’ ተብሎ የተሰየመው ግለሰብ ጋር ነው የሚሄዱት፡፡ ይህ ሂራጋኖ የተደበቀውን ሚስጥር፣ የወንጀሉን አፈፃፀምና ምክንያት ሁሉ የመርመር ሃላፊነት አለበት፡፡ እነዚህ ሰዎች በተፈጥሮ የተሰወረውን በደል የመምርመርና የመተንበይ ተሰጥኦ ከፈጣሪ የተሰጣቸው ነው ተብለው ይታመናሉ፡፡

በተጨማሪም ‘ሂራጎኖ’ዎቹ ከሕይወት ተሞክራቸው በመነሳት መልካም ነገር እንዲፈጠር ልዩ ጥንቃቄ በተሞላ መልኩ ድምዳሜ የሚሰጡ እና በአካባቢው የተረጋጋ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያደርጉ መሆናቸውን ያስረዳሉ። እነዚህ አካላት ፍቅርን የሚያለመልሙ፤ ዘላቂ የሕይወት ተሃድሶን የሚያመጡ ፤ ከጥፋትና ከመጠፋፋት የራቀና ይቅር ባይነትን ባህል ያደረገ ማህበረሰብን የሚፈጥሩ እንደሆኑ የሚታመን መሆኑን ያመለክታሉ። አመዛዝነው ጥልቀት ያለው ውሳኔ የሚሰጡ ግለሰቦች ሰስለመሆናቸውም ይጠቅሳሉ፡፡

**እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ሽማግሌዎች የራጋኖን ውሳኔን በመያዝ በሟች ቤተሰብ ውስጥ ይሰበሰባሉ፤ በውሳኔውና በቀጣይ ሊሆን በሚገባው ጉዳይ ላይ ይመክራሉ፡፡ በዚያ ጊዜ ግን የገዳይ ቤተሰብ አይገኙም**

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ሽማግሌዎች የራጋኖን ውሳኔን በመያዝ በሟች ቤተሰብ ውስጥ ይሰበሰባሉ፤ በውሳኔውና በቀጣይ ሊሆን በሚገባው ጉዳይ ላይ ይመክራሉ፡፡ በዚያ ጊዜ ግን የገዳይ ቤተሰብ አይገኙም። በመቀጠልም ጉዳዩን ለማቀዝቀዝ በመጀመሪያ ፀሎት ይደረግና ቤት ውስጥ እሳት እንዲነድ በማድረግ የዚያን ቤተሰብ ሴት ልጅ በውሃ ታጠፋዋለች፡፡ ቀጥለው ወንዝ በመሄድ የገዳይ ቤተሰብ ከሽማግሌዎች ጋር በአንድ አካባቢ ይሆናሉ፤ የሟች ቤተሰብ ግን ከእነሱ ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ቀድመው መገኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በእለቱ የገዳይ ቤተሰብ ለዚህ ፕሮግራም የሚውል ጥቁር በግ፤ ነጭ ሻማ ፤ ገንዘብ የማዘጋጀት ሃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የሚናገሩት መምህር ግርማ፤ «ገዳይና የሟች ቤተሰብ ወንዝ ውስጥ ገብተው እርስ በርስ ውሃ በመረጫጨት ይተታጠባሉ፡፡ ከእንግዲህ ነገሩ በዚህ ያብቃ ተብሎ ይመራረቃሉ» ይላሉ፡፡ መጨረሻም ጥቁር በግ ይታረድና የበጉ አንጀት ሁለቱም እንዲይዙ ተደርጎ በመሃል ላይ ሸክላ ሰሪ የሆኑ ሴቶች ማርና ቅቤ በመያዝ ገብተው አንጀቱን የሚቆርጡበት ሥርዓት የሚከናወን መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ይህም በሁለቱ ወገኖች መካከል የፍቅር ቃልኪዳን እንጂ የመገዳደል ታሪክ አይኖርም የሚል ትርጓሜ ያለው ሲሆን ፤ የዚህ ጥቁር በግ ደም እንደፈሰሰ በደላቸውም እዚሁ ይፈስስ የሚል አመለካከት ያለው እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

የገዳይ ቤተሰብ ከወንዙ ታጥበው እንደወጡ አዲስና ነጭ ኩታ (ጋቢ) ለሟች ቤተሰብ የሚያለብሱበት ሥርዓት መኖሩንም መምህር ግርማ ይናገራሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር የገዳይ ቤተሰቦች ከነሽማግሌዎቻቸው ጋር በመሆን በቀጥታ ወደ ሟች ቤተሰብ ጋር በመሄድ ትልቅ ነጭ ሰንጋ የሚያርዱ መሆኑን፤ ከዚያ በፊትም ሴቶቹ ጤሪራ (በቂቤ የተዋሃደ የገብስ ቡና) ተዘጋጅቶ ሁለቱን ቤተሰቦች የሚመርቁበት ሥርዓት የሚካሄድ መሆኑንም ይጠቅሳሉ። ሴቶች ደግሞ ሻሜታና ቂቤ አምጥተው በሬው ላይ እንዲቀባ ያቀርባሉ፤ የበሬው ሻኛ ላይ ቂቤ ይደረግና «የእናንተ ነገር ይቀጥል ፤ ክፉ ነገር እንደዚህ ሻሜታ ይደፋ» በማለት ተመራርቀው፤ ያንን ሰንጋ አርደው እየበሉ የሚያነጉበት ሂደት መኖሩን ያስገነዝባሉ፡፡

«በዚህ ሥርዓት በጣም አስደናቂው ነገር ገዳይ የሆነው ሰው ከሟች አባት ጋር አንድ ቡሉኮ ለብሰው አብረው ተቃቅፈው ማደራቸው ነው» የሚሉት ጥናት አድራጊው፤ ከዚያ በኋላ በመሃላቸው የሚኖረው የአባትና የልጅ ግንኙነት መሆኑን ያነሳሉ፡፡ በተጨማሪም በሁለቱ ቤሰቦች መካከል ቃል ኪዳን የሚታሰር መሆኑን ጠቁመው፤ «ይህም ቃል ኪዳን እርስ በርስ ላለመዋሸት፤ ላለመሰራረቅ፤ በሃሰት ላመስከር ሲሆን የሚኖራቸውም ግኑኝነት የአባትና የልጅ ስለመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ነው የሚያደርጉት» ይላሉ፡፡

ዝምድናቸው የቱንም ያህል ቢጠናከር ግን በመካከላቸው ጋብቻ ፈፅሞ የተከለከለ መሆኑን ይናራሉ። ከጋብቻ ውጪ ግን ዝምድናቸው እስከለተሞታቸው የሚቀጥል መሆኑን አንስተው፤ « የሟችን ቤተሰብ ይጦራል፤ ያርሳል፤ ሴት ልጆቻቸው ደግሞ እንሰት ይፍቃሉ፤ ህፃናት ልጆቻውም የገዳዩን ቤተሰብ ከብት ይጠብቃሉ» በማለት ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም በዓል ሲኖር የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በማሟላት እና ስጦታ በመስጠት ግኑኙነታቸው ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑንም ነው ያብራሩት፡፡

የ’ጢግ-ጉላ’ ሥርዓት አሁንም ድረስ በሃድያ ሕዝብ ከትውልድ ትውልድ የተሻገረ መምጣቱን፤ ይህም ሥርዓት በመኖሩ በቀልና መጠፋፋት እንዳይኖር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የተፈፀመው እርቅ ዘላለማዊና የማይፈርስ ፤ ሌላ ግድያ የማያስከትል በመሆኑ የህብረተሰቡ መካከል ፍትህና ፍቅር እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ እየተጫወተ ያለው ሚና በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ያመለክታሉ፡፡

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ ይህ ሥርዓት በሃድያ ሕዝብ ትውልዱ እየጨመረና እያደገ በመምጣቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ ግጭት አሁንም ድረስ ይፈጠራል በሕግ አግባብ ፍርድ ጨርሶ ቢወጣም እንኳን ሌላ በደል ወይም በቀል ይፈፀማል፤ ሌላ ደም ያስከትላል ተብሎ ስለሚፈራ ጉዳዩ በሽማግሌዎች ምርቃት እንዲጠናቀቅ ይደረጋል፡፡ የታሰረውም ሰው ቢሆን ይህንን ሥርዓት ሳይፈፅም ማህበረሰቡን ሊቀላቀል አይችልም፡፡ በመሆኑም የፍትህ ሥርዓቱን የሥራ ጫና በማቃለል ረገድ ያለው ፋይዳ እንዲሆም የሀገር ሰላምን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ ተጠናክሮና ተጠብቆ የሚቀይበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

# ወጣቶች

## የወጣት ማዕከላት ለታለመላቸው ዓላማ እንዴት ይዋሉ?

አስናቀ ፀጋዬ



ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በሌሎች የክልል ከተሞች በሚገኙ ወረዳዎች የወጣት ማዕከላት ተገንብተው ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለወጣቱ ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ በተለይ ወጣቶች አልባሌ ስፍራ ከመዋል በእነዚህ ማዕከላት ውስጥ በመገኘት እንደየዝንባሌያቸው በተለያዩ የኪነጥበብ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት፣ ስፖርትና በሌሎችም መስኮች ሲሳተፉ ቆተዋል፡፡ በዚህም ማዕከላቱ በመልካም ስነ ምግባር የታነፁና አካባቢያቸውን ብሎም ከተማቸውን ሊጠቅሙ የሚችሉ ወጣቶችን በማፍራት ባለውለታ ሆነዋል፡፡

በአንድ ወቅት እነዚህ ወጣት ማዕከላት ለወጣቱ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ተጠቃሽ ቢሆኑም ከቅርብ ግዜ ወዲህ ግን ተቀዛቅዘው ቆይተዋል። የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ሲሰጡም አይታዩም፡፡ ወጣቶችም ወደነዚህ ማዕከላት መጥተው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቀስቃሽ በማጣታቸው ተነሳሽነታቸው ወርዷል፡፡ በተለይ ደግሞ በስብዕና ግንባታ ረገድ ማዕከላቱ የሚጠበቅባቸውን ያህል እየሠሩ እንዳልሆነ ይነገራል፡፡

አብዛኞቹም ማዕከላት ከታለመላቸው ዓላማ ውጪ የተለያዩ ስብሰባዎች የሚካሄድባቸውና ልዩልዩ መንግሥታዊ ክንዋኔዎች የሚፈጸምባቸው ከመሆናቸውም ባሻገር አሁን አሁን ቪዲዮ ማሳያዎች፤ የጆተኒና ከረንቡላ ማጫዎቻዎች እንዲሁም አለፍ ሲልም ጫት መቃሚያና የቁማር ውርርድ የሚካሄድባቸው ቦታዎች እስከመሆን ደርሰዋል፡፡

በዚህም ምክንያት የወጣቱን ስብዕና ይገነባሉ ተብለው የታሰቡት እነዚሁ ማዕከላት በተቃራኒው የወጣቱ ስብዕና የሚበላሽባቸው እየሆኑ ብዙ ወላጆችን ምሬት ውስጥ ከተዋል፤ በርካታ ወጣቶችም ወደ እነዚህ ማዕከላት ከመሄድ ለመቆጠብ ተገደዋል፡፡

ይሁንና በአሁኑ ጊዜ የወጣቶች ስብዕና ልማት ዘላቂነትን ለማረጋገጥ የወጣቶች ማዕከላት ቁልፍ ሚና እንዳላቸው በመረዳትና ማዕከላቱ ለዚሁ የስብዕና ልማት ግንባታ እንዲውሉ ለማስቻል በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡ የወጣት ስብዕና ግንባታ ማዕከላትም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን አቅጣጫ በመከተል በተዋረድ በስብዕና ግንባታ ዙሪያ ለመሥራት እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው፡፡

ወጣት ሰለሞን አባተ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ እርሱ እንደሚለው በማዕከሉ የሚኒ ሚዲያ፣ በኤች አይቪ ኤድስ ዙሪያ የምርመራ፣ ምክርና ግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የሥነ ተዋልዶ ጤና፣ የቅድመ ወሊድ መከላከያ፣ የጂምናዚየም፣ የክብደት ማንሳት አገልግሎት፣ ከረምቡላና ፑል የመሰሉ የቤት ውስጥ ጨዋታ፣ የዲ ኤስ ቲቪ፣ ቴይኳንዶ፣ የካፍቴሪያ፣ የቤተ-መጽሐፍት፣የአይ ሲቲ እንዲሁም የጤና ነክ ስልጠና አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡ እነዚህም አገልግሎቶች ወጣቱ በጤና፣ በአካል ብቃት፣በአዕምሮ እንዲበለፅግ ያስችሉታል፡፡ ፑልና ከረምቡላ የመሳሰሉ ጨዋታዎችንና የካፍቴሪያ አገልግሎትን ወጣቶቹ በቋሚነት የሚጠቀሙ ሲሆን ከትምህርት ሰዓት ውጪ ተማሪዎች የቤተ-መጽሐፍት አገልግሎት እስከ ምሽት አራት ሰዓት ድረስ ያገኛሉ፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ ወጣቶቹ በኪነ ጥበብ ዘርፍ በዘመናዊና ባሕላዊ ውዝዋዜ፣ በዳንስ፣ በቲያትር ከትምህርት ሰዓታቸው ውጪ ወደ ማዕከሉ በመምጣት ሥልጠና ይከታተላሉ፡፡ ከዚህ ውጪ በየአስራ አምስት ቀኑ የሥነ-ጽሑፍ ምሽት ያዘጋጃሉ፡፡ በክረምት ወቅት ደግሞ የቪዲዮ ኤዲቲንግ፣ ፊልምና ቲያትር ሥራ ሥልጠናዎችን ይወስዳሉ፡፡ እነዚህንና ሌሎች መሰል አገልግሎቶችን በማዕከሉ ያገኛሉ፡፡

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለፃ አንዳንድ ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ሳቢ አለመሆን፣ በቁሳቁስና በሰው ኃይል አለመጠናከር፣ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች በቂ አለመሆን፣ ለሌላ ተግባርና ዓላማ እየዋሉ መሆን ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር አለመቻል ችግሮች ይታዩባቸዋል፡፡ ይሁንና እንደ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከል እነዚህ ችግሮች አይታዩም፡፡ ለሠራተኞች ደሞዝ ክፍያ ከመንግሥት ከሚወስደው በጀት ውጪ በውስጥ ገቢ ራሱን በራሱ ያስተዳድራል፡፡ የጣልቃ ገብነትና ሌሎች መሰል ችግሮችም የሉም፡፡ ማዕከሉ ለታለመለት ዓላማ ብቻም ነው እየዋለ ያለው፡፡

ይህ ሲባል ግን ማዕከሉ ምንም አይነት ክፍተት የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ የሰው ኃይል እጥረት አለበት፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን አንዳንድ ማዕከላት የተገነቡበት ቦታ ወጣቱን የማይስቡ ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እዛው በወረዳ ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ ይገነቡና ወረዳዎች እነዚህን የወጣት ስብዕና ግንባታ ማዕከላት ለተለያዩ ጉዳዮች የመጠቀም ዝንባሌዎች ይታያሉ፡፡ ነገር ግን የእኛ ወጣት ስብዕና ግንባታ ማእከል ከዛ ወጣ ያለና ማኅበረሰቡ በሚኖርበት አካባቢ ላይ የተገነባ በመሆኑ ያን ያህል የጎላ ችግር አይታይበትም፡፡ እንደውም ማዕከሉ ሌላ አካባቢ ከሚገኙ ማዕከላት የተሻለ ነው፡፡

ከዚህ ውጪ ግን ማዕከሉ በአዲስ አበባ መሳለሚያ እህል በረንዳ አካባቢ የሚገኝ እንደመሆኑ ከጫት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ወጣቶች ግቢው ውስጥ መጠቀም አለብን፣ ኳስ እያየን እንቅማለን ከማለትና የማዕከሉን ንብረት ከመስረቅና መስበር በስተቀር ከራሱ ከማዕከሉ የመነጨ ችግር የለም፡፡ አንዳንዴ ደግሞ በማዕከሉ አስቀድሞ በወጣቶች የተያዙ ፕሮግራሞች እያሉ ለፓርቲ ስብሰባ ቅድሚያ የሚሰጠበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም ወጣቶችን ከማዕከሉ ጋር የሚያቃቅር ችግር ነው፡፡

ዋና ስራ አስኪያጁ እንደሚለው ወጣቱ በሁለንተናዊ መልኩ ስብዕናው እንዲገነባና በወጣቱ ላይ የተለየ ሥራ ለመሥራት ማዕከሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልገዋል። በማዕከሉ ባለው ነገር ግን አንድም በአካል ሁለትም በአዕምሮ የስብዕና ግንባታ ይደረጋል፡፡ ለአብነትም በማዕከሉ ባለው ቤተ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መጽሐፎችን ወጣቶች አንብበው በሥነጽሑፍ፣ በቲያትርና በተለያዩ ክበባት ተሳትፈው ራሳቸውን አልባሌ ቦታ ከመዋል ይታደጋሉ፡፡

ለአብነትም ከዚሁ ከማዕከሉ የወጡ ወጣቶች በባላገሩ አይዶል ተሳትፈው ተወዳዳሪ የሆኑ ወጣቶች ተፈጥረዋል፡፡ በብሔራዊ ትያትር ጨረታ አሸንፈው በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ የውዝዋዜ ትርኢት በማሳየት ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻው ገቢ እያስገኙ ያሉም ወጣቶች አሉ፡፡ ወጣቶቹ እንዲህ አይነቱ እድል ባይመቻችላቸው ምንአልባትም አላስፈላጊ ነገሮች ውስጥ የሚገቡበት እድል ሰፊ ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ወጣቶቹን ስብዕና ለመገንባት ከክፍለ ከተማው ጋር በመነጋገር በማይንድሴት ላይ ያተኮሩ ሥልጠናዎች እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ስብዕና ግንባታን ማዕከል አድርገው ወደ ማዕከሉ የሚመጡ ወጣቶች ጥቂት ናቸው። በዚሁ የስብዕና ግንባታ ዙሪያ ሥልጠናዎች ሲዘጋጁም ፍላጎቱ ኖሯቸው ወደ ማዕከሉ የሚመጡ ወጣቶች የሉም። አብዛኛዎቹ ወደ ማዕከሉ የሚመጡ ወጣቶች አገልግሎት ፈላጊዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ካፍቴሪያ ውጪ ካለው ገበያ በጣም ቅናሽ በመሆኑ አብዛኛዎቹ ወጣቶች በማዕከሉ ባለው ካፍቴሪያ መገልገል ምርጫቸው ያደርጋሉ፡፡ እግር ኳስ በዲ ኤስ ቲቪ ለማየት፣ ፑልና ከረምቡላ ለመጫወት ወደ ማዕከሉ ይመጣሉ፡፡

ነገር ግን ደግሞ የወጣት ስብዕና ግንባታ ማእከሉ በተለይ በራሱ የፌስ ቡክ ገፅ፣ቲክቶክ አካውንትና በሚኒሚዲያ አማካኝነት ትምህርት አዘል መልክቶችንና በማእከሉ ያሉ አገልግሎቶችን ለወጣቶቹ በማስተዋወቅ የስብዕና ግንባታ ስራ ይሰራል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ታዲያ ማዕከሉ የሰለጠነ የሰው ሃይል በተለይ ደግሞ በስብዕና ግንባታ ዙሪያ እውቀቱ ያለውና ሥልጠና የሚሰጥ ባለሙያ የለውም፡፡ በዚህ ዙሪያ ማዕከሉ እየሠራ ያለውም ከተለያዩ አካላት ጋር በስልክም በአካልም አነጋግሮ በመጥራትና ሥልጠና እንዲሰጡ በመጋበዝ ነው፡፡

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ የወጣቶች ዘርፍ አማካሪ ወይዘሮ የሺወርቅ አያኖ እንደሚሉት የወጣቶችን ስብዕና ለመገንባት የወጣቶች ማዕከላት ያላቸው ጠቀሜታ የጎላ ነው፡፡ ለዚህም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የአስር ዓመት የልማት እቅድን መሠረት በማድረግ የዘርፉን እቅድ አዘጋጅቶ ከወትሮ በተለየ መልኩ አጋርነትን በማጠናከር በተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ወደ ተግባር ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ በበጀት ዓመቱም ከተያዙት እቅዶች አንዱ የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላትን አስመልክቶ ሀገር አቀፍ የንቅናቄ መድረክ ማካሄድ ነው። ንቅናቄውን ማካሄድ ያስፈልገበት ምክንያትም የስብዕና ልማት ማዕከላት ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉና ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

ማዕከላቱ ለወጣቶች የእውቀት፣ የክህሎት፣ የስራ ፈጠራና የመገናኛ አገልግሎት እየሰጡ ቢሆንም በተለይ ማዕከላቱን ወደ ማኅበራዊ ኢንተርፕራይዝ ከማሳደግና የስብዕና ልማት ግንባታውን በዘላቂነት ከማረጋገጥ አንፃር ሥራዎች በትኩረት ሊሠሩ ይገባል፡፡ ማዕከላቱን ለወጣቶች ስብዕና ግንባታ ለማዋልና ወደ ማኅበራዊ ኢንተርፕራይዝ ለማሳደግ በክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመስክ ምልከታና የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡

በዚህም ማዕከላቱ ከተደራሽነት አኳያ የተሻለ ቢሆኑም ከግንባታ ዲዛይን፣ ከይዞታ ማረጋገጫ፣ ከባለቤትነት፣ አገልግሎት ጥራት፣ ከበጀትና አስተዳደር አንፃር ሰፊ ክፍተት አለባቸው፡፡ ወጣቶች በአካልና በአዕምሮ እንዲዳብሩ ብሎም የተሟላ ስብዕና እንዲኖራቸው ከማድረግ አኳያም የባለድርሻ አካላት ድጋፍና ክትትል አናሳ ነው፡፡

አማካሪዋ እንደሚሉት እነዚህ ችግሮች ለመፍታትና የወጣቶች ማዕከላት የተሻለ የስብዕና ግንባታ ልማት አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ እንዲሁም በቂ ገቢ ማመንጨት እንዲችሉና ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ብሎም የይዞታ ማረጋገጫ ባለቤትነት እንዲኖራቸው መርሐ ግብር ተዘጋጅቶ ሀገር አቀፍ ንቅናቄ በቅርቡ ተካሂዷል፡፡ ንቅናቄው ውጤታማ እንዲሆንም የዘርፉ አካላት የድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

የወጣቶች ስብዕና ልማት ግንባታቸውን በማሻሻል፤ ሳቢ በማድረግ፣ በቁሳቁስና በሰው ኃይል በማጠናከር እንዲሁም በሚሰጧቸው አገልግሎቶች በቂ ገቢ በማመንጨት የበጀት አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ዘላቂነት ያለውና ለወጣቶች ስብዕና ልማት ግንባታ አስተዋፅዖ እንዲበረክቱ የማኅበራዊ ኢንተርፕራይዞች እሳቤን ማስረፅና በዚህ መርሕ እንዲመሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ስብዕና ግንባታ ዴስክ ኃላፊ አቶ አብዱለጢፍ መሐመድ በበኩላቸው እንደሚናገሩት ንቅናቄው ማዕከላቱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ፣ የተሟላ የስብዕና ግንባታ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻልና ለሌላ አገልግሎት የዋሉ የወጣቶች ማዕከላት ወደ ወጣቶች እጅ ተመልሱ ለተገነቡበት ዓላማ እንዲውሉ ለማድረግ ያስችላል፡፡

የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላት ግንባታቸውን በማሻሻል ሳቢ እንዲሆኑ አለመደረጉ፣ በቁሳቁስና በሰው ኃይል በማጠናከርና በሚሰጡ አገልግሎቶች በቂ አለመሆን፣ አንዳንድ ማዕከላት ለሌላ ተግባርና ዓላማ እየዋሉ መሆናቸውንና የይዞታ ማረጋገጫ የሌላቸው መሆኑ፣ በራሳቸው ከመንግሥት የሚደረጉ ድጋፎች እንደተጠበቀ ሆኖ ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩና በዘላቂነት በሶሻል ኢንተርፕራይዝ እሳቤ እንዲንቀሳቀሱ አለመደረጉና ገቢያቸውን ለማሻሻል የተደረገው ጥረት በቂ አለመሆኑ ከችግሮቻቸው ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ በሆነ መልኩአለመገንባታቸውናአገልግሎት አለመስጠታቸውም እንደ አንድ ችግር ይጠቀሳል፡፡ ከዚህ አንፃር እነዚህን ችግሮቻውን ለመፍታት ንቅናቄው ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ለዚህም የባለድርሻ አካላት ትብብር ወሳኝ ነው፡፡

# የምድር በረከት

# ‹‹በማዕድን ዘርፉ ወደተጨባጭ ሀብት ሊቀየር የሚችል እድል አለ››

*የማእድን ሚኒስትር ዴኤታ*
*አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ*



**ስምስም ምንግሥቱ**

የኢትዮጵያ መንግሥት በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር አመት መሪ እቅድ የእድገት ማእዘኖች በሚል ከያዛቸው አምስት ዘርፎች መካከል አንዱ የማዕድን ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል:: ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት ተከትሎም በማእድን ሚኒስቴር በኩል ተቋማዊ የአደረጃጀት ለውጥ/ሪፎርም/ ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል::

ሚኒስቴሩ በማእድን ጥናትና ልየታ፣ ልማት፣ አቅም ግንባታ፣ ወዘተ. ላይ ሰፋፊ ስራዎች እየተደረጉ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ:: በሌላም በኩል የቴክኖሎጂ አቅም ውስንነት፣ ሕገወጥ የወርቅ ግብይትና የመሳሰሉት የዘርፉ ተግዳሮቶች መሆናቸውም እየተገለጸ ይገኛል::

በዛሬው የምድር በረከት አምዳችን ሚኒስቴሩ ሪፎርም ካደረገ በኋላ ያከናወናቸውንና እያከናወናቸው የሚገኙ ተግባሮችን እንዲሁም ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት እየተደረጉ ባሉ ጥረቶች ዙሪያ ከማእድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ይዘን ቀርበናል። መልካም ንባብ::

**አዲስ ዘመን፡- ሚኒስቴር መሥሪያቤቱ በወሰዳቸው የማሻሻያ (ሪፎርም) እርምጃዎች ያመጣቸውን አበይት የሚባሉ ለውጦችን ቢገልጹልን?**

**አቶ ሚሊዮን፤** ኢትዮጵያ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር ስኩዌር ስፋት ያላት ትልቅ ሀገር ናት:: እንደ ወርቅ፣ ፕላቲኒየም፣ ኒኬል፣ ኮባልት፣ ብረት፣ ለማዳበሪያ ግብአት የሚውሉ ፖታሽ፣ ፎስፌት፣ የድንጋይ ከሰል፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ፣ የእንፋሎት ኃይል፣ የመሳሰሉ ከፍተኛ የሆነ የማዕድን ሀብት ክምችት አላት:: ይሁን እንጂ የሀብት መጠኑ ወይንም የማዕድን አለኝታው በውል በዝርዝር ተጠንቶ አላለቀም:: እስካሁን ባለው መረጃም የኢትዮጵያ ሥነምድር መረጃ ካርታ ከ25 በመቶ አይበልጥም::

ወደ ጥያቄው ስመለስ፣ በመንግሥት በኩል የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በብዙ ዘርፎች ላይ የተመሰረተ ማድረግ ያስፈልጋል የሚል የእይታ ማሻሻያ ተደርጓል::የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የዛሬ አምስት ዓመት ካጋጠመው የኢኮኖሚ መንገራገጭ አንጻር ሲነጻፀር በመንግሥት የተወሰደው የማሻሻያ እርምጃ ትክክለኛ ነው::በሚቀጥሉት አስር ዓመታት የኢኮኖሚ መሠረት ተብለው የተለዩት ግብርና፣ ማዕድን፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ቱሪዝም፣ እነዚህን የሚያስተሳስራቸው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ናቸው::

ከዚህ መነሻ አንድም ውጤት ነው ብለን የምንወስደው ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት የእድገት ደረጃ ሰፊ የሆነ ሀብት ያስፈልጋታል:: ለዚህ የሚያስፈልግ ሀብት እንምጣ ከተባለ ደግሞ ኢንቨስትመንትን በማጠናከርና ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ያለንን የተፈጥሮ ሀብት ማልማት ነው የሚለው ትክክለኛ እይታ ነው::በዘርፉ ላይ ለዘላቂ ልማት ጥሩ በር እንደተከፈተ አድርገን ነው የምንወስደው::

በሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ በዘርፉ ላይ ለመሰማራት ያለው ፍላጎት የተሻለ ሆኖ መገኘቱ አንዱ ውጤት ነው:: ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የተሻለ የመዋቅር ማሻሻያ ወይም ሪፎርም አድርጎ ተልእኮውን ሊወጣ በሚያስችለው መልኩ ራሱን ዝግጁ ማድረጉም ሌላው ውጤት ነው:: ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኢትዮጵያ ለሰነቀችው ልማትም ሆነ ብልጽግና ተልእኮ ከተሰጣቸው ተቋማት መካከል አንዱ በመሆኑ ተስፋ የሚሰጥ ጅምር ውስጥ ይገኛል::

በእስካሁኑ ሥራ እንደ ስኬት ከሚጠቀሰው አንዱ ዘርፉ በራሱ እንደ አንድ የኢኮኖሚ ምሰሶ መመረጡ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በየደረጃው ያሉ ተሳታፊዎች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ መነሳሳትን ፈጥሯል:: ለማገልገል መነሳሳት የፈጠረና ለነገ ተስፋ ያለው ዘርፍ እንደሆነ አድርጎ እንዲወሰድ አስችሏል:: እነዚህ ሁሉ እንደ ውጤት ይወሰዳሉ::

በ2013 በጀት ዓመት መንግሥት የፖሊሲ ለውጥ በማድረግ በወርቅ ምርት ግዥ ላይ የወሰደው እርምጃ ወርቅ ከወደቀበት የምርት መጠን አንሰራርቶ ከስድስት መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቶም ነበር:: ይህን ውጤት ከማስጠበቅ አንጻር በኋላ ላይ ችግሮች ቢያጋጥሙም ችግሮቹ ጊዜያዊ ናቸው ብለን እንወስዳለን:: የጌጣጌጥ ማዕድናትን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ፣ የውጭ ኩባንያዎች በእንፋሎት ኃይል ላይ ለመሰማራት ያላቸው ፍላጎት መጨመርና ሌሎችም የፖሊሲ ለውጦች መነሳሳትን በመፍጠራቸው ስኬቶች ተደርገው ይወሰዳሉ::

**አዲስ ዘመን፡-የማሻሻያ እርምጃው ኢንቨስትመንትን ከመሳብ አንፃር ያስገኘው ውጤት እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የዘርፉ የልማት ሥራ እንደ ግብርና እና ሌሎች የልማት ሥራዎች አይደለም፤ ይለያል:: ሀገርን የሚለውጡ ትላልቅ ውጤቶች ለማስመዝገብ ጊዜ፣ ከፍተኛ ገንዘብ እንዲሁም ትእግሥት ይጠይቃል:: ከጊዜ አንፃር የማዕድን ፍለጋው 15 ዓመትና ከዚያም በላይ ጊዜ ሊወስድ ይችላል:: ትእግሥት ይጠይቃል ያልኩትም ከዚህ አንፃር ነው:: ወደ ልማት ለመግባትም የኢኮኖሚ አዋጭነቱ ቀድሞ ይታያል:: በገንዘብ ደረጃም ቢሆን በብዙ ሚሊዮን ዶላር ወጪ ይጠይቃል። ይህን ሁሉ ማሟላት የሚችል ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል::

ኢንቨስትመንትን ለመሳብ በተከናወኑት ተግባራት በእንፋሎት ኃይል ወይንም ጂኦተርማል፣ በሲሚንቶ ማምረት፤ በአጠቃላይ ወደ 60 የሚሆኑ ኩባንያዎች በተለያየ የማዕድን ልማት ሥራ ላይ ይገኛሉ:: በሥራ ላይ ከሚገኙ ኩባንያዎች 13 የሚሆኑት በወርቅ ማዕድን ልማት ላይ የተሰማሩ ናቸው:: ከነዚህ ውስጥ ወደ ሶስት ኩባንያዎች በሁለትና ሶስት ዓመት ጊዜ ማምረት እንደሚጀምሩ ይጠበቃል::

አንድ የሲሚንቶ ኢንዱስትሪ ለመገንባት በቢሊዮን የሚቆጠር ካፒታል ያስፈልጋል:: አሁን ባለው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ግዙፍ የሆኑ ወደ ሶስት የሲሚንቶ ኢንዱስትሪዎች በግንባታ ላይ ይገኛሉ:: በተለያየ ምክንያት ምርት አቋርጠው የቆዩ የሲሚንቶ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲገቡም ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ሥነምድር መረጃ ካርታ ከ25 በመቶ በላይ እንዳልሆነ ጠቅሰዋል:: ከተጠቀሰው መረጃ በላይ ሲሆን ያልቻለበት ምክንያት ምንድነው?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ማህበረሰቡ መገንዘብ ያለበትና በመገናኛ ብዙሃንም መታወቅ ያለበት፤ የሥነምድር መረጃ ካርታ ከሰሩ 50 ዓመትና ከዚያም በላይ የሆናቸው የአፍሪካ ሀገራት አሉ:: ካርታው በቅኝ ገዥዎች ነው የተሰራው:: ኢትዮጵያ ደግሞ በቅኝ የተገዛች ሀገር አይደለችም::

በራስ አቅም ለመሥራት ነው ጥረት የሚደረገው:: ቀደም ሲል ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ሥራው አልተሰራም:: በአሁኑ ጊዜ የጂኦሎጂ ኢንስቲትዩት ለሀገር ጠቀሜታ ያላቸውን የሥነምድር መረጃ ካርታዎች በመሥራት ሚናውን ይወጣል:: ሰፊ ሀገር እንደ መሆኗ ኢንስቲትዩቱ መንግሥት በሚፈልጋቸው የማዕድን ዘርፎች ላይ አተኩሮ እንዲሰራ ነው የተደረገው::

በኢንስቲትዩቱ የማይሸፈነውን በግሉ ባለሀብት ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት እየተደረገ ነው:: ለምሳሌ አንድ ኩባንያ ፍቃድ ተሰጥቶት ወደ ሥራ እንዲገባ ሲደረግ፣ ኩባንያው ፍለጋ ሲያካሂድ እኛ እንደሀገር አካባቢው ላይ ያለውን የከርሰምድር መረጃ የማግኘት፣ እንዲሁም የእኛ ባለሙያዎችና ዩኒቨርሲቲዎቻችን ትምህርት የሚያገኙበትን እድል ይፈጥርልናል:: በሁለቱም በኩል የሚከናወነው በቂ ባለመሆኑ ዘመናዊ አስተሳሰብ ለመከተል ጥረት እየተደረገ ነው::

አካባቢውን ሁሉ ለመሸፈን የሚያስችል ‹‹ኤርቦርን ጂኦፊዚክስ››ን /ከአየር ላይ ሆኖ መረጃ የመሰብሰብ ዘዴ/ ለመተግባር ከሚመለከታቸው የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ጋር እየተነጋገርን ነው:: በሚቀጥሉት ዓመታትም በዚህ ላይ በስፋት መሥራት እንደሚያስፈልግ አቅጣጫ ተይዟል::

በነገራችን ላይ የሥነምድር መረጃ ካርታ መሰብሰብ ብቻውን ግብ አይደለም:: ያለውን ሀብት ለይቶ መረጃ ወይንም ዳታ ማግኘትም ያስፈልጋል:: በዓለም ላይ መነጋገር የሚቻለውም ሆነ ኢንቨስተርን መሳብ የሚቻለው በመረጃ ነው:: የዳታ ክምችታችንን መጨመር አለብን ከሚል እየተሰራ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ልማቱ ያላደገው ቴክኖሎጂ መጠቀም ባለመቻሉ እንደሆነ ይተቻል፤ በእዚህስ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ቴክኖለጂ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ለሥራው ከሚያስፈልግ የሥራ መሳሪያ ጋር ይያያዛል። በዚህ ረገድም ዘርፉን ለማጠናከር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን ትኩረት በተሰጣቸው ዘርፎች ላይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲሰጥ እየተደረገ ነው:: በዘርፉ ላይ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በመለየት ሥልጠናው ተጠናክሮ ይቀጥላል::

ቴክኖሎጂ ማሟላት ብቻውን በቂ ባለመሆኑ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራቱ ወሳኝ በመሆኑ ነው ለዚህ ቅድሚያ የተሰጠው። በተለይ ደግሞ እያንዳንዱ አካባቢ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት መሠረት ያደረገ ሥልጠና የሚሰጥበት ሁኔታም ተመቻችቷል። ለአብነትም ወለጋ አካባቢ የሚገኝ ዩኒቨርሲቲ አካባቢው ላይ ያለውን ማዕድን ለማልማት የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል መሠረት አድርጎ እንዲያሰልጥንና የምርምር ሥራንም ጨምሮ ተልእውን እንዲወጣ ነው የተመቻቸው:: በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች አካባቢያቸውን የሚቃኝ የሰው ኃይል እንዲያፈሩ ይፈልጋል::

ትምህርት ሚኒስቴር መንግሥት ያስቀመጠውን አቅጣጫ ተከትሎ እንዲያስፈጽም ይጠበቃል:: ሚኒስቴሩ የሀገር ሀብትን ማልማት በሚያስችል መልኩ እንዲቃኝ እየተደረገ ነው:: በዘርፉ የሰው ኃይል የማፍራቱ ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በመካከለኛ ደረጃም በቴክኒክና ሙያ ምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎችን ለመፍጠር እንዲቻል በተመሳሳይ ትኩረት ተሰጥቷል:: ለምሳሌ በአማራ ክልል የጌጣጌጥ ማዕድን በስፋት በሚገኝባቸው አካባቢዎች የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች በዘርፉ የተሰማሩትን በቴክኖጂ ታግዘው እሴት የተጨመረበት ምርት ለገበያ እንዲያቀርቡ ለማስቻል ከፍተኛ ድርሻ መወጣት ይችላሉ::

**አዲስ ዘመን፡- የማዕድን ልማቱ በሚከናወንበት ስፍራ የተጠናከረ አደረጃጀት የለም የሚል ትችት ይቀርባል:: በእዚህስ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ዘርፉ ገብቷቸው መዋቅራቸውን ያስተካከሉ ክልሎች አሉ:: ለአብነት አማራ ክልልን ብንጠቅስ እስከ ወረዳ ድረስ የወረደ መዋቅር አለ:: ይሄ የሚያሳየው ዘርፉ ትኩረት ማግኘቱን ነው:: ቀደም ሲል እንዳነሳሁት ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች ግብይቱን ጨምሮ ምን መሰራት አለበት የሚለውን ያግዛሉ:: እንዲህ ያሉ እድሎችን የሚያመቻቹ የተሻለ የማልማት እድል ይኖራቸዋል:: ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ደግሞ ተሞክሮዎች እንዲሰፉ ያግዛል::

**አዲስ ዘመን፡- በሌላ በኩል ደግሞ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር ሳይሆን ባለሙያውን ዘርፉ ላይ ለማቆየት የሚያስችል ነገር አለመኖር ነው የሚል ትችት የሚያነሱም አሉ:: ለእዚህ ምላሽዎ ምንድነው?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ቀደም ሲል ስላለው ማውራት አንችልም። በእኔ እምነት ቀደም ሲል እንደ አሁኑ እንቅስቃሴ አልነበረም። በዘርፉ ላይ የኢንቨስትመንት ፍላጎት እየጨመረ የመጣው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው:: ይሄ ደግሞ ከሰው ኃይል ጋር ይያያዛል:: የሰው ኃይሉም ከዘርፉ ፍላጎት የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግም መዘንጋት የለበትም::

**አዲስ ዘመን፡- የዘርፉ ልማት ሰላም ይፈልጋል:: ነገር ግን በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከነበረው ጦርነትና ካለመረጋጋት ጋር ተያይዞ ዘርፉ መጎዳቱ ይታወቃልና ጉዳቱ እንዴት ይገለጻል? አሁን ደግሞ የተፈጠረው ሰላም በዘርፉ ላይ ምን ተስፋ አሳድሯል?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የፀጥታው ችግር ሲሚንቶ ገበያ ላይ እንዳይገኝ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል:: የሀገሪቱን 21 በመቶ የሲሚንቶ ፍላጎት ያሟላ የነበረው የትግራይ ክልሉ የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ተዘግቶ ቆይቷል:: የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብም እንቅፋት ፈጥሯል::

ጉዳቱ በተለያየ መንገድ የሚገለጽ ቢሆንም፣ የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የመጣው ሰላም ለዘርፉ ልማት ወሳኝ ነው። የማዕድን ልማቱ በሚከናወንባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ጥበቃ እንዲደረግ መንግሥት አቅጣጫ በማስቀመጡ ልማቱ ተስፋ ሰጪ ሆኗል፤ ትልቅ መነቃቃት ተፈጥሯል:: ገና የተሻለ ውጤት ይጠበቃል:: ትላልቅ የማዕድን ማውጫ ቦታዎች በመንግሥት ጭምር ይጠበቃሉ:: ከዚህ አንፃር መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል::

**አዲስ ዘመን፡- በጌጣጌጥና በወርቅ ማዕድናት ላይ የሚታየውን ሕገወጥ ግብይት ለመቆጣጠር መንግሥት ግብረኃል አቋቁሞ ተንቀሳቅሷል:: እርስዎን ጨምሮ የፕላን ሚኒስትሯ በተገኙበት ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገወጥነትን በመከላከል ላይ የተሳለፈ መልእክትም ነበር:: ይህ ስራ ምን ውጤት አስገኘ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** መንግሥት በሀገራዊ ፀጥታ ሁኔታ ላይ ሲወጠር የውጭ ዜጎች ጭምር ከሀገር ውስጥ የጥቅም ተጋሪዎቻቸው ጋር በመመሳጠር የሀገርን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አሳጥተዋል:: በወርቅ ላይ የምርት መቀነስ የተስተዋለው ከባለፈው ዓመት መጋቢት ወር ጀምሮ ነው:: በዚህ ዓመት ችግሩ ተባብሷል::

መንግሥት በሌላ ሥራ ቢወጠርም ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ እርምጃ ከመውሰድ አልተቆጠበም:: ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ላይ ወደ 45 የውጭ ዜጎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርገዋል:: በድጋሚም በክልሉ ለመገኘት ተሞክሯል። ተጨማሪ ሕጋዊ እርምጃ ያስፈልጋል:: ሕገወጥነቱ ዋጋ አስከፍሏል:: ይሄ ግን አይቀጥልም:: ከፍ ባለ የፀጥታ መዋቅር ችግሩን ለመከላከል ጥረት እየተደረገ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የባህላዊ አምራቾችን ምርታማነት ከመጨመር አንጻርና ማነቆዎችን በጥናት ለይቶ እንዲያሳውቀን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር ባደረግነው ስምምነት መሠረት የመጀመሪያ ዙር ጥናት ውጤት አቅርቦልናል:: ጥናቱን መነሻ በማድረግ ለልማቱ የሚያግዝ ቴክኖሎጂ ወይንም የሥራ ማሽን ለአራት ክልሎች አከፋፍለናል:: የተከፋፈለውን ማሽን ከመጠቀም አንፃር ያለውንና ውጤታማነቱ ላይ ደግሞ ሁለተኛው ዙር ጥናት እየተካሄደ ይገኛል::

በጥናት የተለዩትን በእቅድ ውስጥ በማካተት ይሰራል። የዘርፉን ማነቆዎች ለመፍታት፣ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመርና ዘርፉን በእውቀት ለመምራት የሚያስችሉ በመሆናቸው ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሚደረጉ ስምምነቶች ወደ ተግባር ይለወጣሉ::

**አዲስ ዘመን፡- የኦጋዴን ቤዚን የነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ጉዳይስ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** የዚህ ጋዝ መልማት በርካታ ትርጉም ያለው በመሆኑ ልማቱ በከፍተኛ ሁኔታ ይጠበቃል:: የተረጋገጠ ሀብት ነው:: ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር በአሁኑ ጊዜ ለማልማት የተለያዩ ሀገሮች ኩባንያዎች ፍላጎት እያሳዩ ነው::ዓለም አቀፍ አስተማማኝ ኩባንያ ይጠበቃል:: መንግሥትም እየደገፈው ሥራ እየተሰራ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ወደፊት ከማዕድን ዘርፉ ምን እንጠብቅ?**

**አቶ ሚሊዮን፡-** ቀጣይ ተስፋው ብሩህ ሆኖ ይታየኛል። ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ኩምሩክ ላይ ከሁለት ዓመት በኋላ የግንባታው ሥራ እንደሚጠናቀቅ የሚጠበቅ የወርቅ ማዕድን የሚያለማ ኩባንያ ወደ ምርት ሲገባ በአማካይ በዓመት እስከ 9 ቶን ያመርታል:: እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ታሪክ ሜድሮክ ኢትዮጵያ ኩባንያን ጨምሮ በአጠቃላይ በባህላዊ ወርቅ አምራቾች የሚመረተው ወርቅ ከስምንት ቶን አይበልጥም። አሁን ግን በአንድ ኩባንያ ከፍተኛ ምርት የሚገኝበት እድል እየተፈጠረ ነው::

ይሄ ሀብት በአንድ ዘርፍ ብቻ የሚገኝ ነው:: በዚህ ላይ የብረት፣ የነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሀብቶችና ሌሎችም ሲደመሩ ያለን የመልማትና የማደግ እድል ተስፋ ሰጪ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭም ይሆናል:: በማዕድን ዘርፉ ወደ ተጨባጭ ሀብት ለመቀየር የሚያስችል እድል አለን::

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ሳደረጉልን ትብብር እናመሰግናለን::**

**አቶ ሚሊዮን፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የነፍሴ ነፍስ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ሁሉም ሰው አመል አለው..መኖርን የሚደፍርበት.. አለመኖርን የሚሸሽበት፡፡ የእኔም አመሌ እሷ ናት..ቀይዋ ዝምተኛዋ ሴት፡፡ የነፍሴ ነፍስ ናት..በመኖሬ ውስጥ ያለሁ። ከዳናዬ ተጣብቃ፣ ከታሪኬ ተጋምዳ ባለሁበት ያለች፡፡ ፍቅሯን ነው የምተነፍሰው፣ ዝምታዋን ነው፣ ሴትነቷን ነው የማዜመው..

ቀይ ናት..ረጅም..ጠበብ ብሎ ብዙ ነገሮቹ የተስተካከሉለት ፊት አላት፡፡ መስከረም የጠባበት የሚመስል፣ እንደ ፀደይ ወራት ብራ የሆነ ሴትነት፡፡ ጠበብ ባለ ፊቷ ላይ ውበታም አይኖች፣ ሊደፈጠጥ ብሎ ለትንሽ የተረፈ አፍንጫ፣ ጾም የሚያስገድፍ ከንፈር ከየትኛውም ጥበበኛ ስዕሎች በላይ ነፍስ ዘርተው ይታያሉ፡፡ ሁልጊዜ በግንባሯ ግራና ቀኝ ከአናቷ የወረዱ ሁለት የጸጉር ዘለላዎችን አያለሁ፣ በሌላ ቀን ደግሞ ጸጉሯን ወደ ኋላ አሲዛ ሌላ ሆና ነው የማያት፡፡ አይኖቿ ሰው ደፍረው ማየት አይችሉም፡፡ ቅርቧ ካለ ሰው ጋር ካልሆነ ሩቅ ካለ ሰው ጋር መዛመድ አትችልም፡፡

ለሁለት ዓመት አንድ ቢሮ ውስጥ ስንሠራ አውርተን አናውቅም..ግን ነፍሴ የእሷን አንደበት እንደናፈቀች ምንም ናፍቃ አታውቅም፡፡ ዝምተኛ ናት..ከዛ ሁሉ እልፍ የሰው ጫጫታ መሐል የእሷ ዝምታ ነው የሚሰማኝ፡፡ ዝም ብላ ሳያት..ዝም ያለውን እግዜር ትመስለኛለች፡፡ እግዜርን የምቀናበት በዝምታው ነው...እሱን አድርጎ ሠርቷት ይሆን እንዲህ የምቀናባት? ስል ራሴን የእብድ ጥያቄ እጠይቃለሁ፡፡

ስሟን አላውቀውም፡፡አጠገቤ ያለን አንድ ሰው ብጠይቀው ስሟን ሊነግረኝ እንደሚችል አውቃለሁ ግን ስሟን ማወቄ ያን ያክል አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ ትቼዋለሁ፡፡ አንድ ቀን ምን እንዳሰኛት እንጃ ያለወትሮዋ ጉርድ አድርጋ መጣች፡፡ ነፍሴ በሴት ልጅ ውበት አቅም ያጣችው ያኔ ነው እላለሁ፡፡ ሴት ልጅ መች አደከመችህ ላለኝ ያን ቀን አስታውሰዋለሁ፡፡ ያን ቀንና ያን ጉርድ እንድትለብስ ያሳሰባትን ሀሳቧን አንድ ላይ ረገምኳቸው፡፡ ርግማኔ ደርሶ ይሆን እንጃ ከዛን ቀን በኋላ ያን ጉርድ አልደገመችውም፡፡ በነጋታው ልብሷን ቀይራ በሱሪ አየኋት፡፡ ያን ቀን በጉርድ ያየሁት ሴትነቷ ዛሬም ድረስ ውስጤ አለ፡፡ ለአፍታ ሞቼ የነቃሁበት፣ ላመል የአለመኖርን አዘቅት ያየሁበት ቅጽበት ያ የእሷ በጉርድ ባጠገቤ ማለፍ ነው ስል ጀሮ ላለው ሁሉ አወራዋለሁ፡፡ ድንገት ነው በአጠገቤ እልፍ ያለችው። ያ እልፍታ፣ ያ ሽውታ ነፍሴን አብሮ ከዛ ውብ ገላና ጠረኗ ጋር ወስዶብኛል፡፡ ውብ እግር፣ ውብ ባት ከጸዳ ቆዳ ጋር እንደመስተዋት ዓይኔ ላይ ሲያንጸባርቁብኝ ነበር ከጣለችብኝ የፍቅር ድንዛዜ የነቃሁት፡፡

ከዛ ቀንና ከዛ ጉርድ በኋላ ላወራት እንደሚገባኝ አሰብኩ፡፡ ይሄን ባሰብኩ በሠልስቱ ሊፍት ውስጥ ተገናኘን። ሳያት ሰማይን ጀርባዬ ላይ ያዘልኩት ያህል ነፍሴ ታውካ ነበር፡፡ ደግሞም የትም ደስ ያላለኝ ደስታ ተዋሕዶኝ ነበር፡፡ ከምትወዳት ሴት ጋር አንድ ሊፍት ውስጥ አብሮ መቆም ደስታው ምን ያክል እንደሆነ አልደረስኩበትም፡፡ የመድረሻ ቁልፌን ልጫን እጄን ወደ ሊፍቱ ስዘረጋ እሷም ስትዘረጋ እጆቻችን ተገናኙ፡፡ ነፍሴ ውስጥ የሆነ ኃይል ተሰማኝ፡፡ እግዜር ያቺን ለአስራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የኖረችውን ሴት በልብሱ ጫፍ ፈውሶ ኃይል ከኔ ወጣ እንዳለው እኔም ስነካት ከእሷ ወደእኔ የተላለፈ ኃይል ጎብኝቶኝ ነበር፡፡ያን ንክኪ፣ ያን መደነቃቀፍ በሕይወቴ ከመጡ ከብዙ መልካም ዕድሎች ጋር አንዱ አድርጌ ቀላቀልኩት፡፡

የፈለገችውን ቁልፍ እንድትጫን እድል ሰጥቼ እጆቼን ሰበሰብኩ፡፡ እኔ ከምሄድበት በአንድ ዝቅ ብላ ቁልፉን ተጫነችው፡፡ ፊት ለፊት መተያየት ስላልቻልን በመስታወቱ ውስጥ አሻግሬ በደንብ አየኋት፡፡ ያልደረስኩበት ሌላም ውበት እንዳላት ተረዳሁ፡፡ በቅርበት ውብ ናት፡፡ እስከዛሬ ያላሸተትኩት ውብ ጠረኗን ያን ቀን ተዋሐድኩት፡፡ ለአይኖቼ ሩቅ የሆኑ ቅንድቦቿን፣ የአይኖቿን ሽፋል፣ በአፍንጫዋና በከንፈሯ መሐል ያለውን ጉብታ ሌላም ዋጋ የሌላቸው የሚመስሉ ብዙ ነገሮቿን አየኋቸው፡፡ምንም ነገር አልተቀባባችም ከንፈሯ ራሱ በተፈጥሮ ወዙ ነው፡፡ ሁሉ ነገሬን ተረድታ የምትከታተለኝ መሰለኝ፡፡ የሕይወቴ እውነት እኮ እንደእሷ ያለች በሥርዓት ውስጥ ያለችን ሴት መወዳጀት ነው፡፡ ከሕልሜ ትልቁ እኮ እንደ እሷ በዝምታዋ የምታምርን ጨዋ ሴት መቅረብ ነው፡፡ የምፈልገው ነገር ሁሉ ያላት ሴት ናት፡፡ ብዙ ሴቶች ላይ ፈልጌ ባጣሁት ውበትና ልዕልና ልታጠምደኝ የተላከች ወይም ደግሞ ፈጣሪ ጸሎቴን ሰምቶ አፍንጫዬ ስር ጣለልኝ ስጦታዬ መሰለችኝ፡፡ የቱን እንደማምን ግራ ገብቶኝ የሊፍቱ በር ተከፍቶ ቀድማኝ ወረደች፡፡ ጠረኗ ሊፍቱ ውስጥ ቀርቶ የምሄድበት ድረስ አደረሰኝ፡፡ ሴት ልጅ እንደዛ ውብ ውብ ስትሸት እሷንና ጥቂት ሴቶችን ነው የማውቀው፡፡

እንደዛ ቀን ክፉ ምኞት ተመኝቼ አላውቅም፡፡ሊፍቱ ተበላሽቶ ወይም የትኛውም ባለሙያ ባልተረዳው እክል መሄድ አቁሞ እኔና እሷ እዛ ሊፍት ውስጥ ውለን ብናድር ስል ተመኘሁ፡፡ ይሄ በሆነ በሁለተኛው ቀን እኔ ደረጃ ስወርድ እሷ ደረጃ ስትወጣ ተገናኘን፡፡ በአይኔ ሰላም ብያት በአይኗ ሰላም ብላኝ ተላለፍን፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በዛ ሁኔታ ሰላም ተባባልን፡፡ ከሄድኩበት ስመለስ ቀጥታ ወዳለችበት በመሄድ ‹ዮናታን እባላለው› ስል እጄን ለትውውቅ ዘረጋሁላት፡፡

‹ፍሬ ሕይወት፡፡ስትል እጄን ጨበጠችው፡፡ ከዛ ሊፍት በኋላ እጆቻችን ዳግም ተገናኙ፡፡ ከእጇ ወደነፍሴ የሆነ ሙቀት፣ የሆነ ትኩሳት፣ የሆነ ንዝረት ተላለፈ፡፡ ‹ግን እኮ እንተዋወቃለን ራሳችንን ማስተዋወቁ ለምን አስፈለገ? ስትል ከአይኔ ሸሽታ ትጽፍበት የነበረውን ኮምፒውተር እያየች ጠየቀችኝ፡፡ ዝምታዋ አይናፋርነት የፈጠረው ከሆነ እጠላታለሁ ጨዋነት የፈጠረው ከሆነ ደግሞ ላልጠላት አፈቅራታለሁ እያልኩ ከራሴ ጋር ስሟገት የሸሸኝን ዓይኗን ወደ እኔ መልሳ መልሴን ትጠብቅ ጀመር፡፡

‹ተግባቦትና ንግግር የሌለበት ትውውቅ ከትውውቅ አይቆጠርም ብዬ ነው› አልኳት፡፡

‹እ..ነው እንዴ..! አለች፡፡

‹አንድ ነገር እሺ በይኝ! አልኳት፡፡

‹ምን?

‹መጀመሪያ ቃል ግቢልኝ..

‹ምን እንደሆነ ሳላውቅ?

‹ቀላል ነገር ነው..

‹እሺ ምንድነው?

‹ነገ ስትመጪ ጉርድ አድርገሽ እንድትመጪ እፈልጋለሁ..› አልኩኝ የምትለውን ለመስማት በመናፈቅ፡፡

‹ማን ስለሆንክ ነው አንተ የእኔን አለባበስ የምትመርጠው? እኔ በራሷ እውነት ውስጥ የቆመች ሴት ነኝ..ማንም ያን አድርጊ ይሄን አድርጊ የሚለኝ ሴት አይደለሁም እሺ› አለችኝ..

በአንድ ጊዜ ኩስስ አልኩ፡፡ በፍቅሯን የበረታ ግርማ ሞገሴ፣ የፍቅሯን ታቦት የተሸከመ ትከሻዬ በተናገረችኝ አንዲት ቃል ምናምንቴ ሆኑብኝ፡፡ ነፍሴ ከስጋዬ ልትለይ ምንም አልቀራት ነበር፡፡ የሆነ ነገር ማለት ስላለብኝ ‹እንደዛ ለማለት ፈልጌ እኮ አይደለም..

‹ምንም ብትል ፊትህ ላለችው ሴት ጉዳይዋ አይደለም።እሷ የራሷ መንገድ ያላት ሴት ናት› አለችኝ ንዴትና ቁጣ በማይታይበት ፊት፡፡እጇን አገጭዋ ላይ አስደግፋ በደንብ አየችኝ፡፡እይታዋን ፈራሁት፡፡ምን ሊያመጣብኝ ይሆን ስል..

ምንም ይሁን ሰው ላለመጨረስ ሰይጣኗን በዝምታዋ ውስጥ ደብቃ የምትኖር ሴት ናት ስል ስም ሰጠኋት፡፡ ከዚህ ቀን በኋላ አጠገቧ ላልደርስ በማመን ካለችበት ሸሸሁ፡፡

.......

በነጋታው በትካዜ በወደኩበት የሆነ ረፋድ ላይ የሆነ እጅ ትከሻዬ ላይ አርፎ አባነነኝ፡፡ ስዞር እሷ ናት..በጉርድ ቀሚስ፡፡ እያየኋት ወደማላውቀው ዓለም ሸሸሁ፡፡ ቀይ እግር፣ ቀይ ባት፣ ቀይ ቆዳ ከውብ ጠረን ጋር ፊቴ ቆሞ ሳይ ገነት ከነሙሉ ክብሯ ተጠቃላ ፊቴ የመጣች ነበር የመሰለኝ፡፡

‹ትላንት እንደዛ ያልኩህ ለፈተና ነበር..ስላስቀየምኩህ ምሳ ልጋብዝህ› አለችኝ፡፡

ፈገግ ብቻ ነው ያልኩት..እንቢ የምልበት ምንም አቅም አልነበረኝ፡፡ከእሷ ጋር ምሳ ለመብላት ከሰዓት እስኪሆን ብዙ ዘላለማትን የጠበኩ ይመስለኛል፡፡

# ዓለም አቀፍ



## ሁለት የአሜሪካ ጦር ሄሊኮፕተሮች ተከስክሰው ሰዎች መሞታቸው ተሰማ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በአሜሪካዋ ኬንታኪ ግዛት ሁለት የጦር ሄሊኮፕተሮች ተከስክሰው ሰዎች መሞታቸው ተሰማ።

የግዛቲቷ አስተዳዳሪ አንዲ በሽያር "የሄሊኮፕር አደጋ መድረሱ እና ሞትም እንደሚጠብቁ መግለጹ ከባድ ዜና ነው" ብለዋል።

ክስተቱ በሀገሬው ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ ሃያ አምስት ጉዳይ ለአራት እንዳጋጠመና እስከ ዘጠኝ ሰዎች መሞታቸውንም የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች ዘግበዋል። የአካባቢው ጦር ሄሊኮፕተሮቻቸው በአደጋው መከስከሳቸውን አረጋግጠዋል።

የጦር ሄሊኮፕተሮቹ የተከሰከሱት ትልቅ ከሚባለው ፎርት ካምቤል የጦር ሰፈር አቅራቢያ በሚገኘው ትሪግ ካውንቲ መሆኑም ተገልጿል።

ኤችኤች 60 ብላክሃውክ የተሰኙ ሁለት ሄሊኮፕተሮች "በተለመደ የሥልጠና ተልዕኮ በነበሩበት ወቅት" መከስከሳቸውን የፎርት ካምቤል ቃል አቀባይ ለቢቢሲ በላኩት መግለጫ አስታውቀዋል። "የጦር ሄሊኮፕተሩ አብራሪዎችም ሆነ ሠራተኞች ሁኔታ ለጊዜው አይታወቅም" ብለዋል።

"በአሁኑ ወቅት የአገልግሎት አባላቱን እና ቤተሰቦቻቸውን በመንከባከብ ላይ አተኩረናል" ሲሉም አክለዋል። የጦር ሄሊኮፕተሮቹ የመከስከሳቸው ክስተት በምርመራ ላይ መሆኑን እና ተጨማሪ መረጃ ሲገኝም ይፋ እንደሚያደርጉም ተናግረዋል።

የፎርግ ካምቤል የጦር ሰፈር ከትሪግ ካውንቲ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛል። እነዚህ የጦር ሄሊኮፕተሮች የ101ኛው የአየር ወለድ ክፍል አካል መሆናቸው የተገለጸ ሲሆን ይህም በአሜሪካ ጦር ውስጥ ብቸኛው የአየር ጥቃት ክፍልና በዓለም አቀፍ ደረጃ ወደ ግጭት ዞኖች የሚላኩ ናቸው ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ ልጃቸው ሼክ ካሊድ ቢን መሐመድ ቢን ዛይድን አልጋ ወራሽ አድርገው ሾሙ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የዓረብ ኢሚሬትስ ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አምስት ታሪካዊ የተባሉ ውሳኔዎችና አዋጆችን ማሳለፋቸው ተገለፀ።

ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን ካሳለፏቸው 5 ታሪካዊ ውሳኔዎች እና አዋጆች መካከልም አዳዲስ የአመራር ሹመቶች እንደሚገኙበት ታውቋል።

ፕሬዚዳንቱ በትናትናው እለት ባሳለፉት ውሳኔ መሠረትም የዓረብ ኢሚሬትስ የፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትን ወንድማቸው ሼክ መንሱር ቢን ዛይድ አል ናህንያን የሀገሪቱ ምክትል ፕሬዚዳንት በማድረግ ሾመዋል።

በዚህም መሠረት ሼክ መንሱር ቢን ዛይድ አል ናህንያን፤ የዓረብ ኢሚሬት ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና የዱባይ ገዢ ከሆኑት ሼክ መሐመድ ቢን ረሺድ አል መክቱም ጎን ለጎን በምክትል ፕሬዚዳንትነት ያገለግላሉ።

በተጨማሪም ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን የመጀመሪያ ልጃቸው የሆነውን ሼክ ካሊድ ቢን መሐመድ ቢን ዛይድን የአቡዳቢ ልዑል አልጋ ወራሽ አድርገው መሾማቸውም ታውቋል። እንዲሁም ሼክ ሀምዛ ቢን ዛይድ አል ናህንያን እና ሼክ ታህኖም ቢን ዛይድ አል ናህንያን ደግሞ የአቡዳቢ ምክትል ገዢዎች ተደርገው መሾማቸውም ተመላክቷል።

ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን በተጨማሪም የአቡዳቢ ኢሚሬትስ የሥራ አስፈፃሚ



ምክር ቤት እንደገና ለማቋቋም አዋጅ ማስተላለፋቸውም ነው የተነገረው። ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን ባሳለፍነው ዓመት ግንቦት ወር ላይ ነበር የአረብ ኢሚሬትስ ፕሬዚዳንት በመሆን የተሾሙት።

ፕሬዚዳንት ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ አንደኛ ዓመት በዓለ ሲመታቸው በተቃረበበት ወቅት ያሳለፏቸው ውሳኔዎች ሀገሪቱን በተሻለ መልኩ ወደ ፊት ለማራመድ ይረዳሉ ተብሎ እምነት እንደተጣለባቸውም መነገሩን የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው።

# ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እየደገፉ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ መንግሥት የውስጥ ሰላሙን የማረጋገጥ ሥራ ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት አገራት ጋር ያለው ግንኙነት የሰመረና የጸና እንዲሆን በትኩረት እየሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲን ከሰላም ዲፕሎማሲ ጋር አስተሳስሮ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጋር እየሠራ መሆኑንም አክለው ጠቁመዋል።

ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በኋላ ቀሪ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አምባሳደሩ፤ የመሣሪያዎችን ድምጽ ማጥፋት መቻሉ ትልቁ ስኬት ነው መሆኑን ተናግረዋል።

ስምምነቱ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓትና መካከል ተቀራርቦ ለመሥራት ጥሩ ዕድልን ፈጥሯል። በትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር መቋቋምና ሕወሓት ከሽብርተኝነት መነሳቱ የሰላም ሂደቱን ስር እንዲሰድ የሚያደርጉ ጅምሮች ናቸው ብለዋል።

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ሰላም ስትሆን ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተጠቃሚ ስለሚሆን በኢትዮጵያ ያለውን የሰላም ሂደት የበለጠ እያገዙ ነው። በኢኮኖሚም ለማገዝ ትልቅ ፍላጎት አለ። በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ የሚጠይቁ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ነው፤ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው በደንብ እየተሠራበት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰላም ጀማሮ ከግምት ውስጥ በማገባት የአውሮፓ ሕብረት፣ አሜሪካ፣ የአፍሪካ አገሮችና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ወዳጅነታቸው ይበልጥ እንዲጎለብት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑንም አብራርተዋል።

ከአውሮፓ ሕብረት ጋር ያለን ግንኙነት እንዲጠናከር ከሕብረቱ በኩል ፍላጎት መኖሩን ያነሱት ቃል አቀባዩ፣ በኢትዮጵያ በኩልም የረጅም ጊዜ የልማት አጋር ከመሆኑ አንጻር ለወዳጅነቱ መጠናከር አበክራ እየሠራች ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ባለፈው አንድ ዓመት 125 ሺህ ኢትዮጵያውያን ከሳውዲ አረቢያ ወደ አገራቸው ተመልሰዋል። እንዲሁም ከምሥራቅና ከመካከለኛው አፍሪካም በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ መደረጋቸውን አምባሳደሩ በመግለጫቸው አንስተዋል።

የዓባይ ግድብን አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ ኢትዮጵያ የመልማት መብቷን ለማረጋገጥ የማንኛውንም አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅት ይሁንታን አትጠይቅም ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብን የጀመረችው ለሙከራ ሳይሆን አጠናቅቆ ለመልማት ነው ብለዋል።

ግድቡ የሚገነባው ብርሃን ለማግኘት፣ እናቶች በወሊድ መሞት ስለሌለባቸው እና እንጨት ከመሸከም መውጣት አስፈላጊ መሆኑን አንስተው ከዚህ ውጪ በሆነ መልኩ በሀሰት የሚሰራጩ መረጃዎች ተቀባይነት የላቸውም። ግድቡ ሲጠናቀቅም ጥቅሙ ከኢትዮጵያ አልፎ ለግብጻውያንና ሱዳናውያንን ጭምር ነው ብለዋል።

እየወጡ ያሉ መረጃዎች አራተኛው የውሃ ሙሌት ስለደረሰ ብቻ የሚወጡ መረጃዎች መሆናቸውን ያነሱት አምባሳደር መለስ፤ ጉዳዩን ዓለም አቀፍ አጀንዳ የማድረግ ጽኑ ፍላጎት እንዳለ ተናግረዋል። ኢትዮጵያውያን ባረጀና ባፈጀ የቅኝ ግዛት ውል የመቀየድ ግዴታ የለባቸውም ሲሉም አክለዋል።

# በሥራ ዕድል ፈጠራ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ባቀረበው የስምንት ወራት አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ምላሽ የሰጡት በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ነገሪ ሌንጮ እንደገለጹት፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት ይገባል።

ዜጎች ሰርተው እራሳቸውን ለማሳደግ ያላቸው መብት ከዴሞክራሲ ጥያቄ ጋርም ይያያዛል ያሉት ሰብሳቢው፤ የሥራ ዕድል ፈጠራ የማሳደግ ጉዳይ የዜጎችን መብት የማክበር አጀንዳ በመሆኑ ውጤታማነቱን ማሳደግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ነገሪ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ በርካታ ምሩቃን ሥራ ያለማግኘታቸው ጉዳይ የተለየ እይታና ትኩረት ይፈልጋል። በመሆኑም የሥራ አጥነት ችግሩ መጠን እስከምን ድረስ ነው?፤ ችግሩ በአገር ሰላምና መረጋጋት ላይ ያለው አንድምታ ምን ይመስላል? የሚለውን በትክክል መቃኘትና መፍትሄ ማቅረብ ይገባል።

የሰላም ዕድሎችን በመጠቀም ኢንቨስትመንትን ማጠናከርና ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ይገባል። አሁን ያለው አንጻራዊ ሰላም ለኢንቨስትመንት ምቹ በመሆኑ በቀሪው የበጀት ዓመት ጊዜያት ተጨማሪ የሥራ ዕድል የማስፋት ሥራው ሊጠናከር ይገባል ብለዋል።

ሚኒስቴር መስሪያቤቱ የነበሩ ችግሮችን ተመልክቶ በፌዴራል ደረጃ ሳይወሰን ከክልል እስከ ወረዳ ካሉት መዋቅሮች ጋር በመናበብ ለመሥራት ያደረገው ጥረት የሚበረታታ መሆኑን ጠቁመው፤ ቋሚ ኮሚቴው ለሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮጀክቶችና ውጤታማነት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶክተር ቤተልሄም ላቀው በበኩላቸው፤ የቱሪዝም ዘርፉ በርካታ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ያለው አቅም ከፍተኛ በመሆኑ በአግባቡ መጠቀም ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አገርም «ገበታ ለትውልድ» የመሳሰሉ ፕሮጀክቶች እየመጡ ስለሆነ ከቱሪዝም ሥራ ጋር ተያይዞ በስልጠና ብቁ የሆኑ ባለሙያዎችን ለመፍጠርና የሥራ ዕድልን ለማስፋፋት ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅቶች መደረግ እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የሥራ ዕድል ፈጠራውን ለማጠናከር የሚረዱ የተለያዩ ሥራዎች ተከናውነዋል።

በዚህም ባለፉት ስምንት ወራት ለ2 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ2 ሚሊዮን 84 ሺህ 702 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፤ አፈጻጸሙም ከእቅድ አንጻር 82 በመቶ ነው ብለዋል።

በስምንት ወራት ውስጥ ከተፈጠሩ የሥራ ዕድሎች መካከል 41 በመቶዎቹ በአገልግሎት ዘርፍ፣ 19 ነጥብ 7 በመቶ ደግሞ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሲሆን፤ የግብርና ዘርፉ 39 ነጥብ 2 በመቶ የሥራ ዕድል መፍጠሩን አስታውቀዋል።

የሥራ ዕድል ፈጠራው በገጠርና በከተማ ሲታይ 53 ነጥብ 9 በመቶ በገጠር የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሲሆን 46 ነጥብ 1 በመቶው ደግሞ በከተሞች አካባቢ የተፈጠረ የሥራ ዕድል መሆኑን ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ እንደገለጹት፤ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ 6 ሚሊዮን ዜጎች ሥራ አጥ ናቸው። ይህንን ቁጥር ለመቀነስ የተለያዩ አገራዊና ክልላዊ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው እየተሠራም ይገኛል።

# በ10 ዓመታት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ትናንት «እኔ መልዕክት አለኝ» በሚል መሪ ሃሳብ በዘመናዊ ኢነርጂ አቅርቦት እጥረት ምክንያት በሴቶችና ሕፃናት ላይ በሚደርሰው ጫና ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አድርጓል።

በወቅቱ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኢነርጂ አማካሪ አቶ ጎሳዬ መንግስቴ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ እንደገለጹት፤ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ሁሉንም የአገሪቱ ዜጎች የዘመናዊ ኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግ አገር አቀፍ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ተቀርጾ እየተሠራ ይገኛል።

ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ከግድቦች ከሚገኘው የኤሌክትሪክ አቅርቦት፣ በፀሐይ ኃይል ከሚሠሩና ከሌሎች የኤሌክትሪክ አቅርቦት አማራጮችን በመጠቀም ዜጎችን የኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ኃይል አቅርቦት እያገኘ ያለው የማኅበረሰብ ክፍል 48 በመቶ ብቻ ነው። 60 ሚሊዮን ዜጎች የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ለማግኘት እየተጠባበቁ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተጨማሪ 98 ሚሊዮን ዜጎች ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙት እንጨት፣ ኩበት፣ ቅጠልና የመሰል አካባቢን የሚበክሉ ግብዓቶችን ነው። በመሆኑም ለምግብ ማብሰያ የሚሆነውን ግብዓት የሚሰበስቡት እና ምግቡን የሚያበስሉት ሴቶች ናቸው። በዚህም በርካታ ሴቶች ለአካላዊ ጥቃትና ለጤና እክል ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋል ሲሉ አስረድተዋል።

ችግሩን ለማቃለል የሚረዱ በርካታ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶች እየተገነቡ ይገኛል ያሉት አቶ ጎሳዬ፤ በመላ አገሪቱ ኤሌክትሪክ እንዲዳረስ ትልልቅ የማስተላለፊያ መስመሮችና የማከፋፈያ ጣቢያዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

በተጨማሪ ለገጠሩ የኅብረተሰብ ክፍል በየመንደሮቹና በመኖሪያ ቤቱ አካባቢ መካከለኛና አነስተኛ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመሮች በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በኩል እየተገነቡ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዋናው የኤሌክትሪክ መስመር ተጠቃሚ የማይሆኑትን የገጠር ነዋሪዎች በፀሐይ ኃይልና በባዮጋዝ አማካኝነት ኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ በስፋት እየተሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

የዓባይ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍቅርተ ታምር በበኩላቸው፤ ዘመናዊ የኃይል አቅርቦት ለአገሪቱ መሠረታዊ ዕድገት ወሳኝነት አለው። ለዘመናዊ የኃይል አቅርቦት መረጋገጥ የዓባይ ግድብ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል ብለዋል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ ለኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ለቱሪስት መስህብ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ በተጨማሪ ለበርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች የኃይል አቅርቦት ተደራሽ ለማድረግና የሴቶችን ጫና ለመቀነስ ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል።

በዘመናዊ የኢነርጂ እጥረት ምክንያት ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጾታዊ ጥቃት እና የአየር ብክለት የኤሌክትሪክ የኃይል አቅርቦትን በማሻሻል የሚደርስባቸውን ጫና መቀነስ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ሴቶች በዓባይ ህዳሴ ግድብ ላይ እያበረከቱ ያለውን አስተዋጽኦ በማስፋት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የቀጣይ አቅጣጫዎች መሠረት ናቸው። በመሆኑም ግድቡ ተጠናቆ የኃይል አቅርቦት ተጠቃሚ ለመሆን የሀብት ማሰባሰብና የሕዝባዊ ንቅናቄ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል።


# አማራ ክልል

ንብረትነቱ የቃልኪዳን ሳምሶን ተካ የሆነ የንግድ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ኮድ 3-14111 አማ የሆነ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በቀን 26/05/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም የመኪናውን ሰሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በደ/ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ**
**ብቃት ማረ/ቡድን**

# አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ዩኤን ኤች ሲ አር የሰሌዳ ቁጥር የተመ-01-0064 የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር JTEEB71J407037359 ሞዴል HZJ76L-RKMRS የሞተር ቁጥር 1HZ-0877164 የሊብሬ ቁጥር 0197233 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፉብኝ ብለው 20/7/2015 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን**
**የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

ከሳሽ /አመልካች፡- ሰብስቤ ቲምመርጋ ንዳ በተከሳሽ/ተጠሪ፡- ረታ እንዳለ አወቀ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድ ኢንቨ 5ኛ ንግድ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች ተጠዎች በ26/07/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ አቶ እሸቱ አለምዬ እና በተከሳሽ ወ/ሮ ወይንሸት ዘውዴ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ ወ/ሮ ወይንሸት ዘውዱ ለ26/7/2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ/ምድብ 3ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

ሕብረት ባንክ Hibret Bank

**ለአቶ መክብብ ሲራክ ግስላ፣ወ/ሪት ሄለን ገ/ንጉስ ገ/ህይወት፣ ለወ/ሪት መድኃኒት መላኩ መሐሪ " ለወ/ሮ የሮም ከለላው እንዳይላሱ እና ለአቶ ደረጄ ሀይሌ ባዩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፣**

እርስዎ አቶ መክብብ ሲራክ ግስላ ከሕብረት ባንክ አማ ቦሌ መድኃኒያለም ቅርንጫፍ የተበደሩትን ብድር ወቅቱን ጠብቀው ባለመክፈልዎ ምክንያት ያዘጋጀነውን ማስጠንቀቂያ በአድራሻዎ ለማድረስ ጥረት ያደረግን ቢሆንም ልናገኝዎ አልቻልንም፡ በተጨማሪም ወ/ት ሄለን ገ/ንጉስ፣ ወ/ት መድህኒት መላኩ፣ ወ/ሮ የሮም ከለላውና አቶ ደረጀ ሀይሌም ማስጠንቀቂያ ለማድረስ በአድራሻችሁ አላገኘናችሁም። ስለሆነም ይህ ማስጠንቀቂያ በዚህ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ቀሪውን እዳ በጠቅላላው እንዲከፍሉ እያስጠነቀቅን ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለብድሩ በዋስትና ያስያዛችሁትን ተሽከርካሪዎች በሐራጅ ሸጠን ገንዘቡን ለብድሩ መክፈያነት ለማዋል የምንገደድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**ሕብረት ባንክ አ.ማ.**

ሕብረት ባንክ Hibret Bank

**ለአቶ በቀለ ቱፋ ወይም ለሕጋዊ ወራሾች እና ለወ/ሮ ለቺሴ በቃና በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ**

አቶ በቀለ ቱፋ ከሕብረት ባንክ አ.ማ. ሞጆ ቅርንጫፍ የተበደሩትን ብድር በወቅቱ ባለመክፈላቸው ምክንያት ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ለወራሾች ለሚስታቸው ለወ/ሮ ለቼሴ በቃና ወይም ለአስያዥ በአድራሻችሁ ለማድረስ የሞከርን ቢሆንም ልናገኛችሁ ባለመቻላችን ማስጠንቀቂያው ሊደርስ አልቻለም ስለሆነም ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የብድር ዕዳው ተጠናቆ ባይከፈል ባንኩ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለዕዳው በዋስትናነት የተያዘውን ንብረት በሐራጅ ሸጦ ገንዘቡን ለዕዳው መክፈያ ለማድረግ የሚገደድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ሕብረት ባንክ አ.ማ.**

**Amendment on Closing and Opening date for Invitation of Bid Ref No: AAPPPDS/SA/2015/NCB/PIS/02/07/2015**

Addis Ababa City Administration Public Procurement and property Disposal Service (AAPPPDS) has fund with the procuring entity budget to be used for the procurement of Supply, Design, Installation, commissioning and Testing of Network, server room and related Information Technology Infrastructure For Addis Ababa City Justice Bureau was advertised by Addis Zemen Newspaper on April, 20/2023 G.C stated at serial number 3 as Bids will be closed at 11:00 Am/5:00 local time/ and opened the same day at 11:30 Am/ 5:30 local time/ on, April, 20/ 2023 G.C This is amended as Bids will be closed at 11:00 Am/5:00 local time/ and opened the same day at 11:30 Am/ 5:30 local time/ on April, 21/ 2023 G.C at 9th floor Assembly hall.

**For further information please call +251-11-557-31-70**

**Addis Ababa City Administration Public Procurement And property Disposal Service**

# ስፖርት





# የፈረስ ስፖርት አሶሴሽንን ወደ ፌዴሬሽን የማሳደግ ውጥን

ዓለማየሁ ግዛው

ፈረስ በኢትዮጵያውያን ታሪክ ውስጥ ልዩ ቦታ ከሚሰጣቸው የጋማ እንስሳት መካከል ቀዳሚ ነው፡፡ ፈረስ ማለት ለኢትዮጵያውያን የጋማ ከብት ብቻ ሳይሆን መጓጓዣ፣ በበዓላት ጊዜ መዝናኛ፣ ለጦርነት ጊዜ ድምጽ አልባ ታንከኛም ጭምር ነው፡፡

ፈረስ በዘመናችን ተወዳጅና ብዙ ገንዘብ የሚፈስበት ስፖርትም ነው። በእርግጥ የፈረስ ስፖርት በኢትዮጵያም ቀደምት ዘመናዊ የስፖርት አይነቶች አንዱ ነው። ስፖርቱ የተጀመረው በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ሲሆን፤በወቅቱ ለጋሲዮን የሚባሉት (የፈረንሳይ፣ የጣሊያን፣ የእንግለዝና የአሜሪካን) ኤምባሲዎች በግቢያቸው ውስጥ ያዘወትሩት ነበር፡፡ ኤምባሲዎቹ ጃንሜዳ ላይ እርስበርስ ውድድር ሲያደርጉ ንጉሡ ተገኝተው ይመለከቱና ያበረታቱ ስለነበር ኢትዮጵያውን ፈረሰኞችም የባህል ስፖርትን እያከናወኑ ዘመናዊውን በመቅሰም በኋላ ሁለቱም አብሮ በጥምረት እየተከናወነ መቀጠል ችሏል፡፡

ስፖርቱ በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜም በመስፋፋት በተደራጀ መልኩ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ1950 ዓ.ም የፈረስ እሽቅድምድም ተብሎ ተቋቁሟል። በወቅቱ በንጉሡ ትዕዛዝ በባለሙያ ተጠንቶ በአዋጅ ተደግፎ የኢትዮጵያ ፈረስ እሽቅድምድም ተብሎ በመቋቋም ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ስፖርቱ ረጅም እድሜ ቢያስቆጥርም የመንግሥታት ለውጥን ተከትሎ ትኩረት በማጣቱ ተቀዛቅዞ ቆይቷል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የኢትዮጵያ ፈረስ አሶሴሽን ከሃገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን በመፍጠር ስፖርቱን ለማሳደግ የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ይህን ስፖርት ይበልጥ ለማሳደግ የአደረጃጀት ለውጥ በማስፈለጉ ከአሶሴሽን ወደ ፌዴሬሽን ደረጃ ለማሳደግ ሥራዎች መጀመራቸውን ታውቋል። የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ባወጣው የስፖርት ማኅበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት አሶሴሽኑን ወደ ፌዴሬሽን ከፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን የኢትዮጵያ ፈረስ ስፖርት አሶሴሽን አስታውቋል። ይህንን ለማድረግም በተለያዩ ክልሎች ስፖርቱን የሚመሩ አደረጃጀቶችን ለመመሥረት ጥረት እየተደረገ ነው። ለዚህም የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር ድጋፍ ለማድረግ ቃል መግባቱን ከአሶሴሽኑ የተገኘው መረጃ ያሳያል። በዚህም መሠረት በአምስትና ስድስት ክልሎች ስፖርቱን የሚመሩ ፌዴሬሽኖችን በማደራጀት ወደ ፌዴሬሽን ደረጃ ለማሳደግ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።



**የፈረስ ስፖርትን በክልሎች ለማስፋፋት አሶሴሽኑን ወደ ፌዴሬሽን የማሳደግ ሥራ ተጀምሯል፣**

ስፖርቱን ወደ ክልሎች ለማስፋፋት ዘመናዊ የፈረስ ስፖርትን በትርኢት መልክ ለማቅረብ የታሰበ ሲሆን፣ በቅርቡ በአማራ ክልል እንጅባራ ከተማና በኦሮሚያ ክልል ለገጣፎ በተካሄዱ የፈረስ ውድድሮች በመሳተፍና ትርኢቶችን በማሳየት መልካም ግንኙነቶችን ለመፈጠር ተችሏል።

አሶሴሽኑ ወደ ፌዴሬሽን እንዲያድግ መጀመሪያ የውስጥ አደረጃጀቱ መጠናከር እንደሚገባው የተገለፀ ሲሆን፣ አሶሴሽኑ የየክልል ወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎችን በጥምረት በመያዝ እንደሚሠራም አሳውቋል። የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር አሶሴሽኑን ከክልሎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር፣ ቴክኒካልና የፋይናንስ ድጋፎችን በማድረግ እገዛ እንደሚያደርግ ቃል የገባ ሲሆን፣ በክልል ደረጃ ለሚቋቋመው ፌዴሬሽን የመተዳደሪያ ደንብ በማዘጋጀት ድጋፍ ያደርጋል። የሥራ አስፈጻሚ አባላት ምርጫን ደግሞ አሶሴሽኑ የቴክኒክ ድጋፍና የግንዛቤ ማስጨበጥ እገዛን እንደሚያደርግ ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ፈረስ ስፖርት አሶሴሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዘሪሁን ቢያድግልኝ፣ "አሶሴሽንና ፌዴሬሽን ሁለቱም በሕግ ደረጃ እኩል ቢሆኑም፤ ነገር ግን ወደ ፌዴሬሽን ደረጃ አደገ ሲባል የክልሎችን ተሳትፎ ያካትታል" ይላሉ። እንደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ገለፃ፣ የስፖርቱ እንቅስቃሴ እስከ አሁን በአዲስ አበባ ዙሪያ ብቻ ተገድቦ ቆይቷል። በቀጣይ ስፖርቱ እንዲሰፋ በአምስትና ስድስት ክልሎች ስፖርቱን ማዳረስ አሶሴሽኑ ወደ ፌዴሬሽን ማደግ አለበት። ይህም የስያሜ ለውጥ ብቻ አይደለም።

አቶ ዘሪሁን አክለውም፣ አሶሴሽኑ ወደ ፌዴሬሽን ማደጉ የአባላቶቹንና የተወዳዳሪውን ቁጥር ስለሚጨምር ለስፖርቱ መስፋፋትና እድገት እገዛ እንደሚያደርግ ተነግሯል፡፡ በስፖርቱ እንቅስቃሴ ውስጥ አሁን ላይ ስምንት ክለቦች የሚገኙ ሲሆን ስድስቱ በአዲስ አበባና ሁለቱ በኦሮሚያ ክልል ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ በፈረስ ሃብት የታደለችና ከዓለም በስምንተኛና ከአፍሪካ በአንደኛ ደረጃ እንደምትገኝም ያስታወሱት አቶ ዘሪሁን፣ ይህን ሀብት ባሕላዊውንና ዘመናዊው ስፖርት ተጠቅሞ ማሳደግ እንዳልተቻለ በቁጭት ይናገራሉ። ውድድሮችን በስፋት ለማዘጋጀት ስፖርቱን ውድ መሆኑ አንዱ ተግዳሮት ሲሆን፣ ለአንድ ታዳጊ ፈረስ ግዢ በትንሹ አርባና ሃምሳ ሺ ብር ይፈጃል። ፈረሱን ማሰልጠን ጤንነቱን መጠበቅና ሌሎች ነገሮችን ለማሟላትም ከፍተኛ ወጪ ማስፈለጉ ሌላው ፈተና ነው። በመሆኑም እነዚህ ሁሉ ወጪዎች አዳጋች ስለሆኑ ስፖርቱ የሚመራበትን ሕግ ማሻሻል ግዴታ እንደሚሆን አቶ ዘሪሁን ይናገራሉ። እንደሌሎች ስፖርቶች በክለብ ደረጃ ለውድድር የመጣውን ብቻ አባል አድርጎ መቀበል ስፖርቱን ለማሳደግ ስለማይቻል የአባልነት መስፈርት ላይ አንድም ሁለትም ተወዳዳሪዎችን መቀበል እንደሚያስፈልግ አቶ ዘሪሁን አስረድተዋል፡፡

የስፖርቱ ሌላ ችግር የሆነው የማዘውተሪያ ስፍራ እጥረትን ለመቅረፍም ጃንሜዳ ያለውን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለመሥራት ከአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮና ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በጋራ እንደሚሠሩ አቶ ዘሪሁን ጠቁሟል፡፡

## ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ እልፍነሽ ያደታ ተወካይ ሁምነሳ ሁንዴሳ እና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ተወካይ ፈዳሣ ገርባ፣ ጣልቃ ገብ ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት መካከል ያለውን የፍትሐብሔር ክርክር በማስመልከት የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ስላስተላለፈ እናንተም ይህንን በመረዳት በክርክሩ ጣልቃ መግባታችሁን በማወቅ የጽሁፍ መልሳችሁን በመያዝ በቀጠሮ ቀን 29/07/2015 ዓ.ም በ5፡00 ሰዓት ላይ እንድትቀርቡ፤ በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት የማትቀርቡ ከሆነ የጽሁፍ መልሳችሁን የማቅረብ መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ በሌላችሁበት የሚሰማ መሆኑን በመረዳት እንድትቀርቡ የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል።

**በቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ምድብ ችሎት**

ከሳሽ ዳንኤል ራጎ ተወካይ ሁምነሳ ሁንዴሳ እና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር መካከል ያለውን የፍትሐብሔር ክርክር በማስመልከት የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ስላስተላለፈ እናንተም ይህንን በመረዳት በክርክሩ ጣልቃ መግባታችሁን በማወቅ የጽሁፍ መልሳችሁን በመያዝ በቀጠሮ ቀን 28/08/2015 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ላይ እንድትቀርቡ፤ በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት የማትቀርቡ ከሆነ የጽሁፍ መልሳችሁን የማቅረብ መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ በሌላችሁበት የሚሰማ መሆኑን በመረዳት እንድትቀርቡ የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አዟል።

**በቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ምድብ ችሎት**

በከሳሽ አለማየሁ ገመዳ ተወካይ ሁምነሳ ሁንዴሳ እና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር መካከል ያለውን የፍትሐብሔር ክርክር በማስመልከት የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ስላስተላለፈ እናንተም ይህንን በመረዳት በክርክሩ ጣልቃ መግባታችሁን በማወቅ የጽሁፍ መልሳችሁን በመያዝ በቀጠሮ ቀን 28/07/2015 ዓ.ም በ8፡30 ሰዓት ላይ እንድትቀርቡ፤ በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት የማትቀርቡ ከሆነ የጽሁፍ መልሳችሁን የማቅረብ መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ በሌላችሁበት የሚሰማ መሆኑን በመረዳት እንድትቀርቡ የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

**በቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ምድብ ችሎት**

ይግባኝ ባይ የክልል አቃቤ ሕግ እና መልስ ሰጪ አሰፋ በረዛ መካከል ስላለው የሐሰተኛ ገንዘብ ማዘዋወር ወንጀል ክርክር አስመልክቶ የጉጂ ዞን ፖሊስ መምሪያ መልሰ ሰጪን በአድራሻው ፈልጎ ማግኘት አለመቻሉን መልስ ሰጭ በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ መከሰሳቸውን አውቀው ቀጠሮው በ27/07/2015 በ4፡00 ሰዓት ቀርበው እንዲከራከሩ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ደቡብ ምድብ ወንጀል ችሎት**

በከሣሽ የምዕራብ አርሲ ዞን ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት እና
4ኛ አህመድ ጣይብ ለሊሳ 5ኛ ሐቢብ ቦራ ጩሪሶ ከባድ የመግደል ወንጀል አስመልክቶ እነዚህ ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው በቀጠሮ ቀን 28/07/2015 በ 4:00 ሰዓት ላይ ለክርክር እንዲቀርቡ ጥሪውን በእናንተ በኩል እንድታደርጉላቸው እና ይህ ትዕዛዝ በምዕራብ አርሲ ዞን ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት በኩል እንዲፈጸም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አዟል።

**የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ጉዳይ ቡድን**

በከሣሽ የምዕራብ አርሲ ዞን ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት እና 2 ወንዱ በላቸው ይፍሩ 3 ዘባኑ ጀምበሩ ከባድ የመግደል ወንጀል አስመልክቶ እነዚህ ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው በቀጠሮ ቀን በ28/07/2015 በ 8:30 ሰዓት ላይ ለክርክር እንዲቀርቡ ጥሪውን በእናንተ በኩል እንድታደርጉላቸዉ እና ይህ ትዕዛዝ በምዕራብ አርሲ ዞን ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት በኩል እንዲፈጸም የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አዟል።

**የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ጉዳይ ቡድን**

በከሳሽ ዮሐንስ ሹማ ተወካይ ቀናሣ ሻንቆ እና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ተወካይ ፈዳሣ ገርባ፣ ጣልቃ ገብ ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት መካከል ያለውን የፍትሐብሔር ክርክር በማስመልከት የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ስላስተላለፈ እናንተም ይህንን በመረዳት በክርክሩ ጣልቃ መግባታችሁን በማወቅ የጽሁፍ መልሳችሁን በመያዝ በቀጠሮ ቀን 28/07/2015 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት ላይ እንድትቀርቡ፤ በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት የማትቀርቡ ከሆነ የጽሁፍ መልሳችሁን የማቅረብ መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ በሌላችሁበት የሚሰማ መሆኑን በመረዳት እንድትቀርቡ በቀጠሮ ቀን 28/07/2015 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት ላይ እንድትልኩ የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ሹንቃ ጫፎ ተወካይ ቀናሣ ሻንቆ እና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ተወካይ ፈዳሣ ገርባ፣ ጣልቃ ገብ ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት መካከል ያለውን የፍትሐብሄር ክርክር በማስመልከት የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ስላስተላለፈ እናንተም ይህንን በመረዳት በክርክሩ ጣልቃ መግባታችሁን በማወቅ የጽሁፍ መልሳችሁን በመያዝ በቀጠሮ ቀን 28/07/2015 ዓ.ም በ5፡15 ሰዓት ላይ እንድትቀርቡ በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት የማትቀርቡ ከሆነ የጽሁፍ መልሳችሁን የማቅረብ መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ በሌላችሁበት የሚሰማ መሆኑን በመረዳት እንድትቀርቡ የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ችሎት ቡድን**

በከሳሽ ጥላሁን ዋሬ ተወካይ ቀናሣ ሻንቆ እና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ተወካይ ፈዳሣ ገርባ፣ ጣልቃ ገብ ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት መካከል ያለውን የፍትሐብሔር ክርክር በማስመልከት የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ስላስተላለፈ እናንተም ይህንን በመረዳት በክርክሩ ጣልቃ መግባታችሁን በማወቅ የጽሁፍ መልሳችሁን በመያዝ በቀጠሮ ቀን 28/07/2015 ዓ.ም በ8፡15 ሰዓት ላይ እንድትቀርቡ፤ በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት የማትቀርቡ ከሆነ የጽሁፍ መልሳችሁን የማቅረብ መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ በሌላችሁበት የሚሰማ መሆኑን በመረዳት እንድትቀርቡ የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ዮሐንስ ማሎኔ ተወካይ ሁምነሣ ሁንዴሣ እና በተከሳሽ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ተወካይ ፈዳሣ ገርባ፣ ጣልቃ ገብ ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት መካከል ያለውን የፍትሐብሔር ክርክር በማስመልከት የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቤርሞግ የመንገድ ግንባታ ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ስላስተላለፈ እናንተም ይህንን በመረዳት በክርክሩ ጣልቃ መግባታችሁን በማወቅ የጽሁፍ መልሳችሁን በመያዝ በቀጠሮ ቀን 27/07/2015 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት ላይ እንድትቀርቡ፣ በቀጠሮው ቀን እና ሰዓት የማትቀርቡ ከሆነ የጽሁፍ መልሳችሁን የማቅረብ መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ በሌላችሁበት የሚሰማ መሆኑን በመረዳት እንድትቀርቡ የቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል።

**በቄለም ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሄር ምድብ ችሎት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ እና በተከሳሽ አምሳለች ኤራንጎ ወልደዮሀንስ መካከል ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ ወንጀል ችሎት ባለው የኮንትሮባንድ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ25/07/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ ተከሳሽ በቀጣይ ቀጠሮ ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ እና በተከሳሽ አብነት ደምለው ወልዱ መካከል ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ምድብ ችሎት ባለው የማጭበርበር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ25/07/2015 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ ተከሳሽ በቀጣይ ቀጠሮ ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**